# ራ

## የኢትዮጵያ ቀንደኛ ጠላት!

በወርቅአፈራሁ አሰፋ

2009 ዓ/ም

@amharicbooks24 click here

@amharicbooks24 ይሄን ይጫኑ

መጽሐፍት

የተመረጡ አማርኛ ና እንግሊዝኛ
መጽሐፍትን ,ትረካዎችን,ወጎች ያገኛሉ

...

© የደራሲው መብት የተጠበቀ ነው

ኮምፒዩተር ጽሑፍ - ሄለን ታደሰ
መሠረት አስማማው (0913 95-29-81)

የመጀመሪያ እትም —— ሐምሌ 2009 ዓ.ም

# ባላመሰግናችሁ ቅር ይለኛል

- ፈጣሪ መዘናጋቴን አይቶ የምታበረታው፣ አይዞህ የምትለው ረዳት ብሰጠው ወደሚፈልገው እና የተመኘው ግብ ይጠጋል ሲል አሰበ። እናም ሰጠኝ። እንዳለውም የግራ ጎኔ አጥንት አበረታችኛና ስድስተኛ መጽሐፌን እውን አደረግሁ። ይህች ሴት መመስገን የለባትም? እንግዲያውስ በእናንተ በአንባቢዎች ስም አመሰገንኳት። ውድ ባለቤቴ ሄል ፈጣሪ የምትፈልጊውን ሁሉ ያሟላልሽ።

- ወዳጄ አቤል ሠይፈ (አቤሎ) ማመስገኛ ቃል የለኝም። የምለው ይገባሃል አይደል......? እግዜር አብዝቶ ይስጥህ።

- የደብረብርሃን ነዋሪው አቶ ክፍሌ ተሰማ መወለድ ቋንቋ ብቻ እንደሆነ በተግባር አሳይተውኛል። ውለታዎን ፈጣሪ ይክፈልዎ።

# ቅድመ ታሪክ

"ከሀዲዎቹ የሰይጣን ልጆች!" በሚል ርዕስ የፃፈችው መፅሐፍ በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ ባሉ ኢትዮጵያውያን በእጅጉ የተወደደላት ሦስና አለማየሁ ፓልማ ማሉርካ ውስጥ ከሚገኙ እውቅ ቤተ-መጻሐፍት አንዱ በሆነው "Biblioteca Publicade Palma de Mallorca" ተሰይማለች:: በተመስጦ እያነበበች ነው:: የቆመቱ ርዝመትና የትከሻው ስፋት ግዙፍነቱን የሚያሳብቅበት፣ ፀጉሩን ሙልጭ አድርጎ የተላጨ ሰው ወደነበረችበት ሲጠጋ ልብ አላለችም:: ድምጹን ዝቅ አድርጎ

"ሦስና ረቂቁን!?" አላት::

ቀና ብላ ተመለከተችው:: ደገመላት::

"ሦስና ፍጠኚ:: ጊዜ የለኝም"

አይታው አታውቅም:: ካኪ ሱሪ በጥቁር ጉርድ ሸሚዝ ለብሷል:: ትንንሾችና ጉድጓዳቸው ውስጥ የተደበቁ አይኖቹ ጭካኔ ይነበብቸዋል:: ግንባሩ ላይ የተጋደሙት መስመሮች አስቀያሚ ገጽታውን ይበልጥ አበላሽተውበታል:: የላይኛው ከንፈሩ በከፊል ተሰንጥቋል:: ፈራችው::

"ምንድን ነው የምታወራው?" ዝቅ ባለ ድምጽ ጠየቀችው::

"ስለምን እንደማወራ ታውቂያለሽ:: ይልቅ ጊዜ አታባክኚ"

እንዴት አወቁ? ለህትመት ያልበቃ ረቂቅ ነው:: ኮምፒውተር ላይ መፃፍ መረጃ ለማስጠለፍ እና ለአደጋ እንደሚያጋልጥ ጠርጥራ በብዕር ነው የፃፈችው:: ያውም አርቃ ደብቃዋለች:: ማንም ከማይጠረጥረው ሰፍራ:: ፓልማ ውስጥ በተዋወቀችው ፕሮፌሰር ለማካይኑት ኢትዮጵያ ውስጥ

*ወደሚገኝ ደብር ልካዋለች።*

*"ስለምትለው ነገር ምንም አላውቅም"*

*"የአምላካችንን የሉሲፈርን እቅድ እንደዋዛ ማክሸፍ አትችይም"*

*ክፉኛ ደነገጠች። ደርሰውበታል። የነገራቸው ሰው አለ ማለት ነው። ያ ሰው ማነው? የረቂቁን ጅማሬና ፍፃሜ ለማንም ትንፍሽ አላለችም። ታትሞ እንባቢ እጅ እስኪደርስ መናገር አልፈለገችም። ለአንዲያ ልጇም ቢሆን። የሚያውቁት ሦስት ሰዎች ብቻ ናቸው። እሷና መነኩሴው እንዲሁም ፕሮፌሴሩ። መነኩሴው ያሉት ደግሞ ከፓልማ ማሎርካ በ3052.9 ማይል እርቀት ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝ ደብር ነው።*

*"የማውቀው ነገር የለም አልኩህ"*

*ቦታው አልተመቸውም። እርምጃ መውሰድ አይታሰብም። እያጉረመረመና እየዛተባት ወጣ።*

*"አታመልጭንም። በአምላካችን በሉሲፈር ስም እምልልሻለሁ፣ ረቂቁ ታትሞ ህዝብ ዘንድ ከመድረሱ በፊት በቁጥጥራችን ስር እናውለዋለን"*

# -1-

# ስትሬሳ፣ ጣልያን

ኢትዮጵያን በቁጥጥሩ ስር ለማድረግ ከልቡ ቆርጦ የተነሳው ማርዱክ ራ ሉሲፈር ቀኝ እጅ የሆነው ማርዮ ኖኤል ፐሪስኮት ጀሌዎቹን የእንቁላል ቅርፅ ባለው ብርሃናማ አዳራሽ ሰብስቦ ንግግር እያደረገ ነው። የታላላቅ ሀገራት መሪዎች፣ የገዝኛ ሚዲያ ተቋማት ባለቤቶች፣ ስመ-ጥር የፖለቲካ ሰዎች፣ እውቅ የሃይማኖት መሪዎች፣ የፋይናንሱን ዓለም የተቆጣጠሩ ባለሀብቶች፣ የምስጢር ማህበራት ተወካዮች እና አቻዎቻቸው አዳራሹን አጨናንቀውታል። በጽሞና እያዳመጡት ነው።

"እውነት እውነት እላችኋለሁ ይህ ቃል የእውነተኛውና የሦስተኛው ነብይ የማርዮ ኖኤል ፐሪስኮት ነው። የድል አምላክ የሆነውን የጌታዬን የሱፐሪም ሳሜክ ማርዱክ ራ ሉሲፈር እውነተኛ ዓለም አስመልክቼ በፊታችሁ ንግግር ሳደርግ ታላቅ ኩራት ይሰማኛል። መጪው ዓለም የአንድ ዓለም ስርዓትና ሕግ ተግባራዊ የሚሆንበት፣ የኃያላን ኃያል፣ የጌቶች ጌታ የሆነው ማርዱክ ራ በዙፋኑ ላይ ሆኖ መንግስቱን የሚያስተዳድርበት፣ ፍጡራንን የሚገዛበት አዲስ ዓለም ነው። በዚህ አዲስ ዓለም አንድ ሃይማኖት፣ አንድ አምላክ፣ አንድ የመገበያያ ገንዘብ፣ አንድ ቋንቋ ብቻ ይኖራል። ያ ሃይማኖት የጌታዬና የጌታችሁ ሃይማኖት የሆነው ሰይጣናዊ የዓለም አስተዳደር ነው። የመገበያያው ገንዘብ በዓለም ህዝብ ሰውነት ውስጥ በማይክሮ ቺፕስ አማካይነት የምንቀብረው የኤሌክትሮኒክስ ገንዘብ ሲሆን፣ ቋንቋው ደግሞ ጌታዬ ሉሲፈርና ተገዥው የሆነው ህዝብ የሚግባቡበት

የእንግሊዝኛ ቋንቋ ነው፡፡

እቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ እንገዳ የሆነውን የአዲስ ዘመን እንቅስቃሴ በወደፊት የጋራ ቋንቋችን ገለፃ (The Green New Age Movement) መጀመራችንን ታውቃላችሁ፡፡ የሁላችሁም ተሳትፎ ወሳኝ ነው፡፡

"የሳሜክ ማርዱክ ራ ሉሲፈርን አምላክነት የምትገዙት ህዝብ እንዲቀበል ቅስቀሳ ማድረግ ይጠበቅባችኋል፡፡ እልህ አስጨራሽ እንደሚሆን አይጠፋኝም፡፡ ሆኖም ጌታዬና ጌታችሁ ማርዱክ ራ ሉሲፈር የሰጣችሁን ሀብትና ስልጣን ከተጠቀማችሁበት ከግባችሁ መድረሳችሁ አይቀርም፡፡ የክዚህ ቀደሞቹ የህዝብ ሃይማኖቶች ጠፍተው ሰይጣናዊ አስተዳደር እንዲሰፍን መስዋዕትነት ከፈሉ፡፡

"በበርካታ ሀገራት እየተሳካልን ነው፡፡ በምዕራባውያኑ ዘንድ ሰይጣናዊ የአምልኮ ስፍራዎችን መመልከት እየተለመደ መጥቷል፡፡ ህፃናት ለማርዱክ ራ ሉሲፈር እየተገበሩ ነው፡፡ የተመሳሳይ ጾታ ግንኙነት በሃይማኖታዊ ስርዓት ስም እየተፈፀመ ነው፡፡ የአዲስ ዘመን እንቅስቃሴያችን ይህን ሁሉ የሚያካትት ነው፡፡ ይህ እንቅስቃሴ ጥንቆላና አስማትን በእጅጉ የሚደግፍና የሚያበረታታ ነው፡፡ ሃያኛው ክፍለ ዘመን የሽግግር ዘመን መሆኑን ሳልጠቁማችሁ አላልፍም፡፡ ሽግግሩ ከዘመነ ፒሰስ (ክርስትያናዊ የበላይነት) ወደ ዘመነ-አኳርየስ (የአዲስ ዓለም አስተዳደር ዘመን) የሚደረግ ነው፡፡ እውነት እላችኋለሁ የጸረክርስቶስ ዘመቻ አላማን ያነገበው የአዲስ ዓለም አስተዳደር በሃይማኖቶች ላይ የበላይነትን ይቀዳጃል፡፡ የሰው ልጆች ሁሉ መመሪያ ይሆናል፡፡ ይህን እውን ለማድረግ፣ ማርዱክ ራ ሉሲፈርን ለማስደሰት የተጣለባችሁን ህዝብን የማሳመን አደራ በብቃት ተወጡ፡፡ ያኔ ነው የማርዱክ ራ ሉሲፈር እውነተኛ ታዛዦችና አገልጋዮች የምትባሉት፡፡

"አሳጥሬ ማድረግ የሚገባችሁን ልግለፅላችሁ፡፡ ህዝብን በተለይም ሀገር ተረካቢ የሚባለውን ወጣት ሃይማኖት የለሽ አድርጉትና ማርዱክ ራ ሉሲፈር እግር ስር ጣሉት፡፡ ጥንቆላና አስማትን አስፋፉ፡፡ ከተደራጀው ማህበረሰብ ባህል ያፈነገጠ የወሲብ አብዮት አቀጣጥሉ፡፡ ዓለምን



ተቃራኒዎቻችን እግዚአብሔር ብለው የሚጠሩት አምላካቸው ከፈጠረላት መልካም ተፈጥሮአዊ ባህሪዋ አውጥታችሁ በሰይጣናዊ ነውጥ አንሳቁሷት፡፡ እውነት እላችኋለሁ ይህን ካደረጋችሁ ሉፕሪም ሳሜክ ማርዱክ ራ ሉሲፈር ወደዙፋኑ በሚመጣበት ጊዜ ውለታችሁን በማይተመን ዋጋ ይከፍላል፡፡"

ተሰብሳቢዎቹ ፈቃደኝነታቸውን በጋለ ጭብጨባ ገለፁ፡፡ ጭብጨባው ዘለግ ላለ ጊዜ መቀጠሉን የተገነዘበው ማርዮ ፕሪስኮት እጁን ከፍ አድርጎ ካስቆመ በኋላ ንግግሩን ቀጠለ፡፡

"በማርዱክ ራ ሉሲፈር ስም አመሰግናለሁ፡፡ ለማስታወስ እና ትኩረት እንድትሰጡት ለማለት እንጂ የሉሲፈርን አዲስ ዓለም ለማምጣት እየተጋችሁ መሆኑ ጠፍቶኝ አይደለም፡፡ ብዙዎቻችሁ እየተሳካላችሁ እንደሆነ ከሚደርሰኝ ሪፖርት ማረጋገጥ ችያለሁ" አለና በድንገት ዓይኖቹን ጠበብ አድርጎ የትካዜ ዓለም ውስጥ ገባ፡፡ በድንገተኛው ትካዜ የተደናገጡት ተሰብሳቢዎች እርስ በእርሳቸው ተያዩ፡፡ አሁን በአሁን ምን ሆነ? ሲሉ አንሾካሾኩ፡፡ የተከሰተውን ነገር ለማወቅ ጓጉ፡፡

ማርዮ ፕሪስኮት በቀጣይ ንግግሩ የአዳራሹን ድባብ ቀየረው፡፡

"እቅዳችን በተሳካ ሁኔታ እየሄደ ቢሆንም አሳሳቢ ጉዳይ ገጥሞናል፡፡ ወሳኝ መፍትሔ እስካላበጀንለት ልፋታችን ሁሉ መና መቅረቱ ነው!"

"ምንድነው?... ምንድነው?" ሲሉ ተንጫጩ፡፡

"የጌታዬንና የጌታችሁን የማርዱክ ራ እቅድ፣ የእኛንም ልፋት የሚያከሽፍ ዘዴ የተካተተበት ረቂቅ ለሕትመት ተዘጋጅቶ መቀመጡን ደርሰንበታል"

"በሉሲፈር ስም.....!!"

"በማርዱክ ራ ስም!!" መንጫጫቱ አየለ፡፡

"ታትሞ ህዝብ ዘንድ ከደረሰ አለቀልን!"

ማርዮ ፕሪስኮት እውነቱን መሸከም የከበደው ይመስል ልቡን ደገፍ

የሚንጫጩትን ተሰብሳቢዎች ተመለከታቸው።

"ማነው የጻፈው? ፀሐፊውን አድነን እንያዘው!"

"ከመታተሙ በፊት ፈልገን እናቃጥለው!"

"የጌታችን የማርዱክ ራ ሉሲፈር እቅድ በዋዛ አይከሸፍም!"

መፈክር መሳይ ዛቻዎች እና ጥያቄዎች ተኀርጎደጎዱ። መደማመጥ ጠፋ። ተናጋሪ እንጂ አድማጭ ታጣ።

"እባካችሁ ፀጥታ!"

ማርዮ ፕሪስኮት እጁን ከፍ አድርጎ ጮኸ። ፀጥታ እንደሰፈነ

"እኔና የቅርብ ረዳቶቼ ዝም አላልንም። የራሳችንን ሰው ወደፀሐፊዋ ልከናል። ለጊዜው የተጨበጠ ውጤት ላይ ባንደርስም። የምታውቀው ነገር እንደሌለ ሽምጥጥ አድርጋ ትካድ እንጂ ረቂቁን እንደደበቀችው በማስረጃ ደርሰንበታል"

ተሰብሳቢዎቹ በአንድ ድምጽ ጮኹ።

"ፀሐፊዋ ማነች? ጌታችንን የደፈረች ይህች ሴት ማነች?"

ማርዮ ፕሪስኮት መልስ ሰጠ።

"ሶስና አለማየሁ የምትባል ኢትዮጵያዊት ነች"

የጸሐፊዋን ስምና "ኢትዮጵያ" የሚለውን መጠሪያ ከሰሙት ተሰብሳቢ ዎች መሃል አብዛኞቹ እንደማጥወልወል አደረጋቸው። ያለምክንያት አልነበረም። ባለጋራቸው በመለኮታዊ እሳት ከተከበበች ቅድስት ሀገር የወጣች የማትበገር ፀሐፊ መሆኗን አረጋግጠዋል። "ከሀዲዎቹ የሰይጣን ልጆች!" የሚለው መፅሐፏ ምስክር ነው። መለኮታዊውን እሳት ተሻግሮ ወደቅድስቲቱ ሀገር ለመግባት መሞከር የፈተናዎች ሁሉ ፈተና እንደሚሆን አልተጠራጠሩም።

ሁሉም በየእራሱ ሀሳብ በመስመጡ ድምፅ ጠፋ። ሁኔታው በእጅጉ



ካሳሰባቸው ተሰብሳቢዎች መሃል የሞንቴ ካርሎ ምስጢር ማህበር ዋነኛ ተዋናይ የሆነው ሉቺዮ ጂሊ ኮልሸንባች እጁን አውጥቶ እንዲናገር ሲፈቀድለት የድምፅ ማጉያውን ወደአፉ አስጠጋ።

"ፈፅሞ ለማመን የሚያዳግት ነገር እየሰማን ነው። የጌታችንን የማርዱክ ራ እቅድ የሚያከሽፍ ዘዴ ተፅፎ እስኪጠናቀቅ አንቀላፍተናል። የምን ማንቀላፋት ሞተናል እንጂ። የዚህችን ልጅ የቀድሞ መፅሐፍ የማንበብ እድል ገጥሞናል። አካሄዷ እጅግ አደገኛ ነው። ከፋቱ ከእሳት ሀገር መገኘቷ። ውሳኔ ላይ ካልደረስን አትጠራጠሩ ዓለም የሚፈራቸው ታላላቅ ሀገራት እና መንግስታት ያልተቀዳጁትን ድል መቀዳጀቷ አይቀርም። ህዝብን አሳምና፣ በተለይ የሀገሯን ዜጎች ከጎኗ አሠልፋ ዓመፅ ማስነሳቷ ሳይታለም የተፈታ ነው። የድሃ ሀገር ውልድ ስለሆነች እንናቃት። ዓላማችንን ማሳካት የተሳነን እሷ ሀገር ውስጥ ነው። ይህንን ፈተና በድል ሳንወጣ ጭራሽ አሳሳቢ የሆነ ሌላ ፈተና ይዛ ብቅ አለች። የጌታችንን እቅድ የሚያከሽፍ ዘዴ በመፅሐፍ!

"በሞንቴ ካርሎ ማህበር ባለስልጣንነቴ በርካታ ተግባራት ላይ ተሳትፌያለሁ። አንዱን ለማንሳት ያህል አሜሪካ የምትባል ሀገርን ለማጥፋትና በምትኩ የአንድ ዓለም አስተዳደርን ተግባራዊ ለማድረግ የተሳተፍኩበት ዘመቻ ነው። እዚህ ጋር ሰዎች ሲምታታባቸው አስተውላለሁ። አሜሪካ የሚለው ስም ሲነሳ በቀጥታ የሚያገናኙት ከእኛ የሰይጣናዊው ዓለም መሪ ተዋናዮች ጋር ነው። በእርግጥ አሜሪካ አባሎቻችን በሆኑ መሪዎቿ አማካይነት ያበረከተችው አስተዋጽኦ ይኖራል። ያም ሆኖ ህልውናዋ ከእኛ ህልውና አንፃር ሲታይ ኢምንት በመሆኑ ህዝቦቿ በእኛ መስመር እስካልተሰለፉ ለእሷም የማንመለስ መሆናችንን ዓለም ሊያውቀው ይገባል። አሜሪካ ትጥፋ ስንል መሪዎቿ የሚተባበሩን ታማኝነታቸው ከሀገራቸው ይልቅ ለእኛ ማለቱ ለማርዱክ ራ ሉሲፈር እና ለተከታዮቹ በመሆኑ ነው። ወደ ነጥቤ ስመለስ አሜሪካን በአንድ ዓለም አስተዳደር ስር ለማድረግ በተሳተፍኩበት ዘመቻ ያልገጠመኝ ፈተና ነው ኢትዮጵያ ከምትባል ድሀ ሀገር እየገጠመኝ ያለው። ሳምንታዊ መመሪያ

ለመቀበልና ኢትዮጵያ ውስጥ አላማችንን ለማሳካት ስለሚያስችለን ሁኔታ ለመወያየት ለሁለት ዓመታት በየሳምንቱ አርብ ያውም ሳላስተጓጉል ከሌሊቱ ሰባት ሰዓት ላይ የቫቲካን ሲቀጳጰስ ዘንድ ተመላልሻለሁ፡፡ ፊፅሞ ሲሳካልን አልቻለም፡፡ ይህ በእንዲህ እያለ ነው እንግዲህ ይህች አዲስ ክስተት ጋሬጣ እየሆነችብን የመጣችው"

ሉቺዮ ጂሊ ኮልቨንባች ሶስናን "አዲስ ክስተት" እያለ ነው የሚጠራት፡፡ ሉቺፈርን በጦስ፣ ሟርት እና ጥንቆላ ለሚያምነው ሰይጣናዊ መሪ ሶስና ራስ የምታዞር አዲስ በሽታ ነች፡፡ ይህን ኃይሏን ያገኘችው ከየትም ሳይሆን አጥብቃ ከምታምነው ፈጣሪ እንደሆነ ያውቃል፡፡ ለዚህም ነው እየፈራት የሚጠላት፡፡ እሱና መሰሎቹ እንኳን እንደኢትዮጵያ ያለች ድሃ ሀገር ትቅርና በቴክኖሎጂ የተራቀቁ፣ በሀብት ክምችታቸው የመጠቁ ሀገራትን በቁጥጥራቸው ስር ማድረግ እንደማይሳናቸው በተግባር አረጋግጠዋል፡፡ በቴክኖሎጂ የተራቀቁ፣ በሀብት ክምችታቸው የመጠቁ ሀገራት በቁጥጥራቸው ስር ቢውሉም ኢትዮጵያ ግን......እምን ፅኑ እምነቷ ነፃ አውጥቷታል፡፡ ይህን ጽኑ እምነት ለመናድ ነው ትግላቸው፡፡ እንዳይንዱት ሶስና ይሏት ጉድ፣ የምስኪን ሀገር አዲስ ክስተት እቅዳቸው የሚከሸፍበትን ዘዴ የሚያጋልጥ፣ የማርዱክ ራ ሉሲፈርን ፍላጎት እንደጤዛ የሚያረግፍ፣ እንደጉም የሚያበን አዲስ መፅሐፍ......እንዘፈዘፈው ጥርሶቹን እያንቀጫቀጨ ንግግሩን ቀጠለ፡፡

"ይህች ራስ የምታዞር ሴት ከሀዲዎቹ የሰይጣን ልጆች በሚለው የመጀመሪያ መፅሐፏ ከሁላችሁም በላይ መሳቂያ መሳለቂያ ያደረገችኝ እኔን ነው፡፡ መረጃውን ማን እንዳቀበላት ሉሲፈር ይወቅ፡፡ የተከታዮችንን የሂዩንሴ ኖውልስን ጉድ የዘረዘረችበትን ምዕራፍ እንዳጠናቀቀች እኔ ላይ ነበር የዘመተችው፡፡ "ብላክ ማስ" የተሰኘ የሰይጣናዊ አምልኮ ስነ-ስርዓት ላይ ግንባር ቀደም ተዋናይ መሆኔን፣ ርቃኔን መጨፈሬን፣ የህፃን ልጅ ደም መጠጣቴን፣ ኧረ እሷ ጉደኛ ነች፡፡ ከ24 ዓመቱ ወንድ ፍቅረኛዬ ጋር ወሲብ መፈፀሜን...."

እንደመሸኮርመም፣ እንደማፈር አደረገው፡፡

"ይህን ሁሉ ዘርዝራ ፅፋለች፡፡ የፃፈችው ሁሉ አንድም ሀሰት የሌለበት



መሆኑ አይደለም የሚደንቀው፡፡ ምስጢሩን ማን ይፋ አወጣላት? የሚለው ነው አነጋጋሪው፡፡

"ይህች አደገኛ ሴት እቅዳችን የሚከሸፍበት ዘዴ የተካተተበት መፅሐፍ እንደፃፈች ነው እየተነገረን ያለው፡፡ እቅዳችን የሚከሸፍበትን ዘዴ ከፃፈች እቅዳችንን ሙሉ ለሙሉ ደርሳበታለች፣ አውቀዋለች ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችሁ ራሳችሁን ፈትሹ፡፡ እንደኔ ገመናችሁ ለአየር እንዲበተን የምትፈልጉ አይመስለኝም፡፡ ከእኛ ስምና ክብር ይልቅ የጌታችን ማርዱክ ራ ሉሲፈር ስምና ክብር ይበልጣልና እቅዱ ከመክሸፉ፣ ስሙ ከመጥፋቱ እና ክብሩ ከመገፈፉ በፊት መፅሐፉን ፈልገን ማቃጠል ይኖርብናል"

"ትክክል....!....ትክክል!" ሲሉ ተንጫጩ፡፡

"ያለበለዚያ" አለ ሉቺዮ ጂሊ ኮልቨንባች፡፡

"ያለበለዚያ ለሺህ ዓመታት ያህል በግዞት ከቆየበት ዓለም ተመልሶ ነፃ ሊያወጣን በዝግጅት ላይ ያለውን ጌታችንን ሱፐሪም ሳሜክ ማርዱክ ራ ሉሲፈርን ክፉኛ እናሳዝነዋለን፡፡ ይህ እንዲሆን የሚፈልግ አለ?"

"በፍጹም! ኧረ በፍፅም!"

"ስለዚህ ደራሲዋንና አደገኛውን ረቂቅ ለማግኘት ትጉ"

"እንዴታ!"

"የጌቶች ሁሉ ጌታ፣ የድል አምላክ የሆነው ሱፐሪም ሳሜክ ማርዱክ ራ ሉሲፈር ይርዳችሁ"

"አሜን"

"ክብር እና ምስጋና ለማርዱክ ራ ሉሲፈር!"

"አሜን... እልልልል!"

ስብሰባው ተጠናቀቀ፡፡

ኮሚሽን ባለስልጣንነቱ፣ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ኃላፊነቱ፣ የዩኒሴፍ ቀኝ እጅነቱ ተገልያላቸዋል። "ዋ የሰው መጨረሻ!" ሲሉ በመስቀል እየወገሩ የተፀናወተው መንፈስ እስኪለቀው ሊያጠምቁት ቃል ገቡ እንጂ ጤነኝነቱን አምነው፣ የሚናገረው ትክክል ነው ብለው ሰንሰሉቱን ሊያወልቁለት አልፈለጉም። በትርፍ ጊዜያቸው የሚናገረውን ለመስማት ስሜታቸው እንደሚያቆበቁብ አይክዱም። ይቀበሉትም አይቀበሉትም የማለዳ ጩኸቱ ይናፍቃቸዋል።

አሁንም ጆሯቸውን ቀስረው ሊያዳምጡት ተዘጋጁ። ስሜታቸውን ስለተረዳ ፊቱን ወደእሳቸው አዞረ። አንድ አድማጭ በማግኘቱ ተደስቷል።

"አባ የተጎሳቆለችው ዓለማችን በበርካታ ምስጢራዊ ነገሮች እንደተሞላች ያውቃሉ?" ድንገተኛ ጥያቄ አቀረበላቸው።

"እንዴታ.... እንዴታ ልጄ"

"እሺ እነዚህን ምስጢራዊ ነገሮች ሰው እንዳይረዳ የሚጋርደውን ኃይልስ?"

"ክፉው ሰይጣን ነዋ። ሌላማ ማን ይሆናል?"

"ጥሩ! ሰይጣን ይህን የሚያደርገው ለምን ይመስልዎታል?"

"እንዴ የሰው ልጅ ምስጢራዊ ነገሮችን ከተረዳማ እውነቱ ይገለፅለትና ሰይጣንን ወግድ ይለዋል"

"ብራቮ አባ! ገብቶዎታል። ሰይጣንና ሰራዊቱ ሰው ምስጢራዊ ነገሮችን ከተረዳ እሺ ብሎ እንደማይገዛላቸው በማወቃቸው ነው የሚጋርዱበት። ህዝቤም ተጋርዶበታል። የእርኩሱ መንፈሳዊ ዓለም መሪ በስመጥር ባለስልጣናት እየታገዘ ይህን ሴራውን ከሀገሬ እና ከህዝቧ ላይ እንዲያነሳ መጮኽ ከጀመርኩ ቆይቻለሁ። ግና ማን ሰምቶኝ? ጭራሽ እብድ አሉኝ። እኔ እብድ ሳልሆን በሀገሬ እና በህዝቧ ላይ የተሸረበው ሴራ የሚያሳስበኝ ጤነኛ ዜጋ ነኝ። ከባዕዳኑ የሀገሬ ሰው ይባስ። የእርሶ ይባስ። ጤነኝነቴን አምናችሁ ልትቀበሉ አልፈለጋችሁም"

ደነገጡ። መልስ ጠፋቸው። እሱ ቀጠለ።



"አልፈርድብዎትም። አልፈርድባችሁም። ለሀገሬ ሰው ፀአዳ ከለበሰ ሴረኛ ቡትቶ የለበሰ መልካም አሳቢ ነው እብዱ። በድህነት ጫና ክርፋት ክርፋት እየሸተተ እውነቱን ከሚናገር ሀቀኛ ይልቅ የኃጢያቱን ትንፋግ በውድ ሽቶ ለማጥፋት የፈለገ ይመስል በሻኔል ፋይቭ፣ በትሩ ላቭ እና በዶልቼ ጋባና የታጠበ አስመሳይ ነው ንጹህ። አይምሰለን። የትኛውም ውድ ሽቶ የህሊናን ክርፋት የማስወገድ አቅም የለውም። የትኛውም ውድ ልብስ ሰውነታችንን እንጂ ገመናችንን የመደበቅ ስልጣን የለውም። ዛሬ ስልጣኔን እና ስራዬን በገዛ ፍቃዴ ስለተውኩ ተጎሳቁያለሁ። ገቢ አልባ ሆኛለሁ። ጠቁሬያለሁ። ብብቴ የሴትን አፍንጫ ከሚስብ ስፕሬይ ይልቅ ውሃ ከነካው የቆየ ገላ ላብ ስለሚያመነጭ ፍየል ፍየል መሽተት ጀምሬአለሁ። ይህ ሁሉ ምክንያት ሳይሆነኝ ስለሀገሬ እና ስለህዝቤ እውነት ብናገር ማን ሰምቶኝ?

"አብረውኝ የነበሩ የሀገሬ ልጆች ፀአዳ ለብሰው ስለዋሹ፣ ስጋቸውን አስብተው መንፈሳቸውን ስላኮሰሱ፣ በሀገራቸው ላይ ከተሸረበው ሴራ ይልቅ የባዕዳኑ ገንዘብ እና ትዕዛዝ ስለበለጠባቸው በጤነኞች መዝገብ ላይ ሰፍረዋል። በምሁራን ዶሴ ላይ በክብር ተመዝግበዋል። እውነት እልዎታለሁ አባ፤ ከእነሱ አይነት ክብር እብድ የሚለው ስያሜ ይሻለኛል።

"ሰማችሁኝ አልሰማችሁኝ በጩኸቴ እቀጥላለሁ። ሰው ባይሰማኝ አንድ ቀን አምላክ ይሰማኛል። በንጹህ ልብ ለሚጠሩት ቅርብ እንደሆነ አምናለሁ። ደግሞስ ማን ያውቃል? ከባዕዳን ተጽእኖ የተላቀቀ፣ ስለሀገሩ የሚያስብ አዲስ ትውልድ ይፈጠር ይሆናል። አምላክ እስኪሰማኝ፣ ስለኢትዮጵያ የሚቆረቆር አዲስ ትውልድ እስኪነገኝ የእርኩሱን መንፈሳዊ ዓለም ገዢ ሴራ ሳጋልጥ እኖራለሁ እንጂ እንደ ባለቅኔው

*በቃ እማማ÷ እማማዬ*
*መቀነቴ÷ ገመናዬ*
*በቃሁሽ አድባሬ÷ መቅኔ*
*ከእንግዲህስ ሳንቺ መጥኔ*
*አዬ ሳንቺ አዬ ለኔ....*

*ሳዩ እማምዬ÷ ደሀና ዋይ*
*ያሳወረሽ አሳወረኝ÷ ቀን የተጣባብን ስራይ!*
*ሳይኔ ሳይንሽንም ሳያይ...*

ብዬ በተስፋ መቁረጥ መንፈስ አልሰናበታትም። ከልጆቿ በስተቀር ማን አላትና?"

አባ ንቡረዕድ በተመስጦ ከአንደበታቸው ቃላት አወጡ።

እ - እግዚኦ ንስእለከ ወናስተበቁዐከ
እስመ አንተ ቅሩብ ለኩሎሙ እለ ይጼውዑከ

"ምን አሉ አባ?"

እንደሰማቸው ሲያውቁ ደነገጡ። ለእራሳቸው ነበር የተናገሩት። ፈጥነው ፍቺውን ነገሩት።

"አቤቱ እንለምንሃለን÷ እንማልድሃለንም።
ለሚጠሩህ ሁሉ አንተ ቅርብ ነህና"

ባልተለመደ ፈገግታ ትኩር ብሎ ተመለከታቸው። በውስጡ ተስፋ አድሮ ነበር።



# -3-

## ፓልማ፣ ማሎርካ

በአዳራሹ ውስጥ የተሰበሰበው ህዝብ ብዛት የተለየ ስሜት ሳይፈጥርበት መድረኩ ላይ እየተንጎራደደ ንግግር ማድረጉን ቀጥሏል።

"በእኛ የዘመን አቆጣጠር ኤፕሪል 1974 ዓ.ም ሳቲቪያ ውስጥ ከሚገኙ ትምህርት ቤቶች በአንዱ እማር ነበር። በወቅቱ ሳቲቪያ ውስጥ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች «ሬድ ሳቲቪያ ስኩልስ» በሚል መጠሪያ የሚታወቁ ነበሩ። በ11 ዓመቴ ከጣሊያን ወደሳቲቪያ በስደት እንደመጣሁ አስታውሳለሁ። ቤተሰቦቼ አብረውኝ ነበሩ።

"የሰይጣን እምነት ተከታይነቴ ታሪክ እየጎለበተ የመጣው እዚህ ትምህርት ቤት ውስጥ ይሁን እንጂ ውልደቴና እድገቴ የተወለድኩበት ጣሊያን ውስጥ ነው።"

ከአድማጮቹ አንዷ የሆነችው ሦስና አለማየሁ ስሜት ነቃ አለ። እንዲህ አይነት ርዕስ ይመስጣታል። ትኩረት ሰጥታ ስለምትከታተለው ይሆናል። ትንፋሿን ዋጥ አድርጋ መስማት ቀጠለች።

"የካቶሊክ እምነት ተከታይ ስለነበርኩ በዘጠኝ ዓመቴ ቫቲካን ውስጥ ማገልገል ጀመርኩ። የጣሊያኑ የኢሉሚናቲ ማህበር አባል ለመሆን ጊዜ አልፈጀብኝም። የተጠየቅሁትን እየፈፀምኩ የኢሉሚናቲዎችን ሰይጣናዊ ተግባር አወቅሁ። ተለማመድኩ። ታዛዥ ነበርኩና በማህበሩ ከፍተኛ የተባለው ሠላሳ ሦስተኛ ደረጃ ላይ ለመድረስ ማንም አልከለከለኝም

በእድሜ የገፋው ኢሉሚናቲ ሉቺዮ ጎሥሊንግ እልጋ ወራሽ እንደምሆን ቃል ተገብቶልኝ ነበር። በአስራ አምስት ዓመቴ የሞንቴ ካርሎ ማሶኒክ ኤክስኪዩቲቭ ኮሚቴ አባል ሆንኩ። የምስጢር ማህበራቱን አላማና ግብ እንዲሁም ሴራ ለማወቅ ችዬ ነበር። በስልጣን ላይ ስልጣን እያገኘሁ ብመጣም በር ተዘግቶ እና ከዓለም ህዝብ ተደብቆ የሚካሄደው ሰይጣናዊ ተግባር እንገሸገሸኝ። ጥንቆላው፣ ሟርቱ፣ ሰይጣናዊ አምልኮው፣ ህፃናትን ማረዱ ሰላም ነሳኝ። በሰይጣናዊው ዓለም ዋና ተዋናይ ሆኜ ብቆይም በመጨረሻ ንስሀ መግባት በፈጣሪ ዘንድ ዋጋ ሊያስጥ እንደሚችል በመገንዘቤ ማህበሩን ከጀ ወጣሁ።

"የኮበለልኩት የምስጢር ማህበራትን ሴራ የሚቃወሙ ህዝቦችና ፀሐፍት ወዳሉባት ፓልማ ማሎርካ ነው። ዛሬም ድረስ መቀመጫዬ ናት። ከተሰደድኩበት እለት አንስቶ ነገሮች የተመቻቹ ባይሆኑም ከትግሌ አላፈገፈግሁም። ሰይጣናዊ ቡድኖቹ እና አባሎቻቸው እስከሚጋለጡ ወደኋላ አልልም። በተገኘው መድረክ አጋልጣቸዋለሁ። በዚህ አጋጣሚ ይህንን መድረክ ያመቻቹልኝን ዳንኤል ኢስቱሊንን እና ሶስና አለማየሁን ከልቤ እመሰግናለሁ"

ሳይታወቃት ጎንበስ ብላ እጅ እንደመንሳት ቃጣት። ካርሎ ዛጋሚ ውሃውን ጎንጨት አለና ንግግሩን ቀጠለ።

"ማህበሩን ከከዳሁ ጀምሮ ስቃዮችን እስተናግዳለሁ። ጥቃቶች ተሰንዝረውብኛል። ሆኖም አልሸሸሁም። እንደውም ኢሉሚናቲን ከመልቀቄ በፊት ከማምናቸው የልብ ወዳጆቼ ጋር «**The As Hermetis Foundation**» የተሰኘ ድርጅት አቋቁሜያለሁ። ሰይጣኖቹን የኢሉሚናቲ አባላትና ለሰው ልጆች ሁሉ ጦስ የሆነውን ዲያብሎሳዊ ተግባር ለመዋጋት የተቋቋመ ድርጅት ነው። በሂደት ጥሩ ውጤት እንደምናገኝ ተስፋ አለኝ። እዚህ የተገኛችሁ ሁሉ የሰይጣንን እና የተከታዮቹን የምስጢር ማህበር አባላት ሴራ መረዳት ይኖርባችኋል። ያን ጊዜ ነው እውነቱ ተገልጾላችሁ በሙሉ ኃይላችሁ ልትቃወሙት እና አለምን ለማዳን የምትነሱት። በዚህ እሳቤ ወደኋላ ልመልሳችሁ፤ አርባሁለት ዓመት ወደኋላ።



"መግቢያዬ ላይ እንደገለጽኩት በ17 ዓመቴ ላቲቪያ ውስጥ ከሚገኙ ትምህርት ቤቶች በአንዱ ተማሪ ነበርኩ። በወቅቱ እግዚአብሔርን ማምለክ በጥብቅ የተከለከለ ነበር። በምትኩ ተማሪዎች በሰይጣን እንዲያምኑ ይበረታቱ ነበር። እንደክፍል ደረጃቸው ስያሜ ተሰጥቷቸው እንደነበር አስታውሳለሁ። ከአራተኛ እስከ ስድስተኛ ክፍል የነበሩት ተማሪዎች «ትንንሾቹ ሰይጣኖች» የሠባተኛ ክፍል ተማሪዎች «የሰይጣን አሽከሮች» የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች ደግሞ «የሰይጣን ታማኝ ልጆች» በሚል ስያሜ ይታወቁ ነበር። በሳምንት አንድ ቀን ስብሰባ ስለሚኖር ሰይጣንን ተመስለው ቀንድ እና ጭራ አድርገው እንዲገኙ ይገደዳሉ። ስብሰባው ሲጠናቀቅ በሰልፍ ይሆኑና በከፍተኛ ድምጽ እንዲህ ሲሉ ይጮሀሉ።

«ሰይጣን አባታችን ሆይ ፈጥነህ ድረስልን። ከአንተ ሌላ አምላክ አናውቅም። እግዚአብሔር የድህነት፣ የፍርሃት፣ የግብዝነት፣ የጥፋት ተምሳሌት እንደሆነ የነገርከንን አልዘነጋነውም። በልባችን ላይ ጽፈነዋል። ለዚህም ነው ድህነትን፣ ፍርሃትን፣ ግብዝነትን እና ክፋትን አባረህ ደስታ የምትለግሰንን አንተን ማምለካችን። አንተ ባለህበት ደስታና ፈንጠዝያ አለ። አንተ ባለህበት ወሲብ እና እርካታ አለ። አንተ ባለህበት ጭንቀት የለም። አንተ ባለህበት ጥጋብ እና ድሎት አለ። ስለዚህ ደስታ፣ ፈንጠዝያን፣ እርካታን እና ጥጋብን የሰጠኸንን አምላካችንን በታማኝነት ስናመልክህ ለመኖር ቃል እንገባለን። ክብር ለአንተ ይሁን!»

ሦስና ደጋግማ አማተበች። ሌሎቹም ካርሎ ዛጋሚ በሚነግራቸው በእጅጉ ተደንቀው ነበር። ዛጋሚ ቀጥሏል።

"በወቅቱ ከሶቭየት ሕብረት ጋዜጦች አንዱ የሆነው ኮሚዩኒዝማ ኡዝቫራ (***Kommunisma Uzvara***) እግዚአብሔርን የካዱ ክበቦች እንደ አሸን መፍላታቸውን ቢጽፍም የተለወጠ ነገር አልነበረም። ይሄ ሁሉ ኮምኒዝምን የፈጠሩት ሠይጣን አምላኪዎቹ ኢሉሚናቲዎች ሴራ ነበር። በአምላካቸው ሰይጣን መመሪያ መሰረት ፈጣሪን የሚክድ ትውልድ ማፍራት እና የንጹሃንን ደም ማፍሰስ ስለነበረባቸው አድርገውታል። ሴራው ዘመን ተሻግሮ ዛሬ ላይ ደርሷል። ዛሬም በእግዚአብሔር የማያምን፣ ሰይጣንን የሚከተል ትውልድ እንዲበዛ እየተሰራ ነው። ሀገራት ትኩረት ተደርጎበታል።

ሐረጎቻችንን ህይወት እስከወዲያኛው የሚለውጥ ነው"

"ፍጠን ማለት አማርኛ አይደለም እንዴ?" ሌላኛው ፖሊስ ቁሱን ትእግስት በማጣት ስሜት አመናጨቀው።

"ደሞስ ምንድነው የምታንሾካሹከው?"

አሁን የሚያስቆየው ምክንያት የለም። ለልጁ መንገር የነበረበትን ነግሮታል። ፖሊሶቹን ተከትሎ ወደምትጠብቃቸው መኪና ሲገባ ከመያዙ በፊት ከ«ሰዎቹ» ጋር የተነጋገረው ትዝ አለው።

"ወንጀለኝነትህ ተደርሶበታል። ግንኙነታችን ከመቋረጡ በፊት ሀገርህ ውስጥ ላሰብነው ተልዕኮ..."

"አታስቡ። እኔ ብያዝም ልጄን እተካላችኋለሁ። የአባቱ ልጅ ስለሆነ በብቃቱ፣ በታዛዥነቱ እና በታማኝነቱ ጥርጣሬ አይግባችሁ። በቋንቋ ችሎታውም አይታማም"

እርግጠኛ ነበር። በልጁ ላይ ፍጹም የሆነ እምነት አለው። ከበርካታ ውሽሞቹ በምስጢር በየቦታው ካንጠባጠባቸው መሃል ከፍተኛ እምነት ያለው በዚህኛው ላይ ነው። እንዴት እንዳሳደገው ያውቃል። ምንም ሳያጎልበት። ግን ከቃሉ እንዳይወጣ አድርጎ።

ልጅም በአባቱ ላይ ያለው እምነት እንደብረት የጠነከረ ነው። ለእሱ የአባቱ ቃል የእግዚአብሄር ቃል ነው። ፈጽሞ የማይሻር። በደም ብቻ ሳይሆን አብዛኛውን ጊዜ በአመለካከትም አንድ መሆናቸውን የሚያውቀው «ወንጀለኛ» ቄስ ረዥምም ጊዜ ቆይታ ወደሚያደርግበት እስር ቤት ሲሄድ ልጁ ትእዛዙን እንደሚፈጽም በሙተማመን ነበር።

***

የሰዎቹን አድራሻ ደጋግሞ ተመለከተ። ስልክ ቁጥራቸውና ኢ-ሜይላቸው ከአጭር የማንነት መግለጫ ጋር። ለጊዜው የሚፈልጉትንም ወሳኝ ነገር አስፍረዋል። አስቸኳይ ተልዕኮ። በማንነት መግለጫው ውስጥ

አላማቸውን መገመት አላቃተውም። ከዚህ ቀደም አባቱም ነግሮታል። አባቱ ደጋግሞ እንዳስገነዘበው የሰማዩን ቤት ማንም አላየውም። ከትውልድ ትውልድ በቃል እና በጽሁፍ ሲተላለፍ የመጣ ማረጋገጫ አልባ እምነት ነው። ገነትም ሲኦልም እዚሁ ምድር ላይ ናቸው። ምርጫው የነዋሪው ግለሰብ ነው። እምኖ ለመቀበል ስለፈራ ውስን ጥያቄዎችን ለአባቱ እንዳቀረበ ያስታውሳል።

"እርግጠኛ ነህ አባ ሰማይ ቤት የሚባል ነገር የለም?"

"የጅሎች ድርሰት ነው አልኩህ እኮ። እንኳን ሰማይ ቤት ፈጣሪ የለም"

ወባ እንደያዘው ሰው ቢንዘፈዘፍም፣ የአባቱን ጤነኛነት ቢጠራጠርም፣ በቅዠት ዓለም ቢዋልልም ትንፋሹን አጠራቅሞ በጥያቄው ገፋ።

"ፈጣሪ ያለመኖሩን ካመንህ...?"

"እንዴት ቄስ ሆንክ ልትለኝ ነው? መሆንና ማመን የተለያዩ ነገሮች ናቸው። በህይወት ዘመንህ አንድ ነገር እንድትገነዘብ እፈልጋለሁ። ዓለም የየዋሆች እና የእድለ ቢሶች ሳትሆን የብልጦች እና የእድለኞች መሆኗን። የዋሆች እና እድለ ቢሶች ምን ጊዜም ቀጥተኛውን መንገድ ይዘው መንዝዝን የሚመርጡ ናቸው። ግን ደስታን እንደናፈቋት ሳያገኟት ያልፋሉ። ብልጦቹስ? በብልጠታቸው እድልን ወደእነሱ ስላቀረቡ በቁስ በልጽገው፣ ተደስተውና ህይወትን አጣጥመው ይሞታሉ። እኔ የእነዚህን መንገድ ከሚመርጡት ውስጥ የምመደብ ነኝ። የምፈልገውን ኑሮ እስክኖረኝ፣ በአቋራጭ ወደምመኘው የህይወት ግብ እስኪደረሰኝ አይደለም ቄስ እርኩስ መንፈስ ለመሆን ፈቃደኛ ነኝ። ገና ለገና ስሞት ሲኦል እገባለሁ ብዬ የምድር ደስታዬን አላጨልመውም። ብልጦች የዋሆች እድላቸውን እንዳይሻሙ የሚያስፈራሩበት መንገድ ነው እምነትና ሃይማኖት። ለእኔ መንፈሳዊው ህይወት አቋራጭ መንገድ ነውና ቄስ ተብዬ፣ ልብስ ተክህኖ ለብሼ በየዋህ ምዕመናን ዘንድ እየተከበርኩ..."

ልጅ በመንታ መንገድ ላይ ቢሆንም ወደአባቱ እምነት አዘንብሏል።

በአስመሳይ ዓለም ውስጥ መንገዝ። አባቱ ሞጋች ጥያቄ አንስቶለት ነበር።

"የተማርከው ፈጣሪ ደግ መሆኑን ነው ወይስ ክፉ?"

"በቃላት የማይገለፅ ደግነት ተምሳሌት መሆኑን"

"ደግ አባት ልጆቹ በጦርነት እንዲረግፉ ይፈልጋል?"

"በፍጹም!"

"እስከዛሬ በዓለም ላይ በተከሰቱ ጦርነቶች ምን ያህል ሰዎች ህይወታቸውን አጥተዋል?"

"እጅግ በጣም ብዙ"

"ፈጣሪ ካለ ለምን አላዳናቸውም?"

ልጅ አማተበ። መልስ አልነበረውም። አባት ሌሎች ጥያቄዎችንም አስከተለ።

"ፈጣሪን አጥብቀው የሚፈልጉትና ከደጁ ሠላም የማይጠፉት ምን አይነት ሰዎች ናቸው?"

"ሀብታሞች ቢኖሩም በቁጥር ምስኪኖች እና ጎስቋሎች ይበዛሉ?"

"ዓለም የእሱ እስከሆነ፣ መስጠት እስካልተሳነው አጥብቀው የሚፈልጉትን ለምን በድህነት ያጎሳቁላቸዋል?"

ልጅ ለሁለተኛ ጊዜ አማተበ። መልስ አልነበረውም። ሌላ ጥያቄ ለማስተናገድ ፈቃደኛ ባለመሆኑ አባቱን ተማፀነው።

"እየሀ የብዙዎች ችግር ይህ ነው" አለ አባት። "በተጠየቀ ሳይሆን በጭፍን ማመን"

አባትና ልጅ ይህን ውይይት ካደረጉ በኋላ ልጅ ከህሊናው ጋር ብዙ ተሟግቷል። ሁሉም የእምነት አባቶችና ካህናት እንደአባቱ «የሰይጣን ቁራጮች» እንዳልሆኑ ያውቃል። ፈጣሪያቸውን በእውነተኛ ፍቅር በታማኝነት የሚያገለግሉ አባቶችን አይቷል። በፈጣሪ እምነት



ተጠምቀው ለሰው ልጆች ጸጋ በረከት በየገዳማቱ ማንነታቸውን የሰጡ መናንያንን ገድል ያውቃል።

ከእራሱ ጋር ብዙ ከተሟገተ በኋላ ውሳኔ ላይ ደረሰ። የአባቱን ሀሳብ ሙሉ በሙሉ ሳይቀበልና ከፈጣሪ ሳይሸሽ ሀብት ንብረት የሚያስገኝ አጋጣሚ ሲገኝ በእድሉ ለመጠቀም። አንዳንድ የሃይማኖት አባቶችና ካህናትም የሚያደርጉት ነው ሲል እራሱን ለማሳመን ሞከረ። ፈጣሪን እንደ አባቱ ሽምጥጥ አድርጎ አይክደውም። ግን ህይወት የሚለውጥ ጥቅም እስካስገኘለት አባቱ ካገናኘው ሰዎች ጋር....ግፋ ቢል ንስሃ መግባት ነው። ስንቱ ቄስ የሚሊዮን ብሮች መኪና እየነዳ አይደል?... በሚሊዮን ብሮች በተገዛ ቪላ እየኖረ አይደል...!? «በእድሉ እጠቀምበታለሁ» አለ ለራሱ። ሰዎቹን እስከሚያገኛቸው ቸኮለ።

## -5-

## ፓልማ፣ ማሎርካ

"በእርግጥ ወስነሻል?" አላት ፕሮፌሰሩ በፍቅር እና በስስት እየተመለከቷት፡፡ እሷ ቤት ነበሩ፡፡ አድራሻ ተሰጣጥተው ከተለያዩ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ መገናኘታቸው ነው፡፡ እንደየአቅማቸው ለሀገራቸው አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ በአንድ መስመር ላይ ተሰልፈዋል፡፡

"አዎ ፕሮፌሰርበውስጥ አዋቂው ካርሎ ዛጋሚ መረጃ የዳሰሰውን ረቂቁን ከማሳተሜ በፊት በተጨማሪ ሀሳቦች ላዳብረው እፈልጋለሁ፡፡ ሉሲፈር በሀገሬ ላይ የሸረበውን ሴራ ማክሸፍ የምችለውም ስለሀገሬ ይበልጥ ሳውቅ ነው፡፡ ወጣቱን ማስተማር የምችለውም ስለኢትዮጵያ የእግዚአብሔር ቤትነት፣ የእምነት ደሴትነት በቦታው ተገኝቼ ሳረጋግጥ ነው"

"ኢትዮጵያን በደንብ ታውቂያታለሽ? የምታርፊበት ዘመድ አለሽ?"

"ሀሳብ የሆነብኝ እሱ ነው፡፡ ሆቴል ተቀምጬም ቢሆን ዓላማዬን ከግብ አደርሳለሁ እንጂ የማውቀው ዘመድ እንኳን የለኝም"

ኢትዮጵያ አንድ ጊዜ ብቻ እንደሄደችና መቼ እንደሄደች እስከምክንያቱ ነገረችው፡፡

ፕሮፌሰር ነብዩ ቶሎሳ በሆቴሉ ሀሳብ አልተስማማም፡፡ በማታውቃት ሀገር ብቻዋን እንድትንከራተት አልፈለገም፡፡ የሰዎቹ ትኩረት ናት፡፡ የሚያስፈልጋት ሰወር ያለ ስፍራ ነው፡፡ ጥሞናዋን ሰብስባ ስራዋን የምትሰራበት፡፡ በጨዋታቸው መሃል ሰዎቹ የአምላካቸው ሴራ



የሚከሸፍበትን ረቂቅ ድርሰት ማዘጋጀቷን እንደደረሱበት ነግረዋለች፡፡ የመፍትሔ ሀሳብ ነው ብሎ ያመነበትን ሀሳብ አቀረበ፡፡

"ሶስና ሆቴል አታርፊም፡፡ ለደህንነትሽም አስተማማኝ ስላልሆነ አይታሰብም"

"ምን አማራጭ አለኝ ፕሮፌሰር?"

"ከከተማ ራቅ ያለ ደብር ውስጥ የሚኖሩ አባት አሉ፡፡ የቅርብ ዘመዴ ናቸው፡፡ እሳቸው ዘንድ እልክሻለሁ፡፡ መረጃ በማግኘቱም በኩል ይረዱሻል፡፡ ለጥናትና ምርምርሽ ትክክለኛ ቦታ ነው"

ደስ አላት፡፡ ያልጠበቀችው እድል ነው፡፡ ለስራዋ ምቹ የሆነ ስፍራ እንደሚሆን ተማምናለች፡፡

"አመሰግናለሁ ፕሮፌሰር"

"የዜግነት ግዴታዬ ነው፡፡ ደብሩ የሚገኘው ሰንዳፋ ከሚባለው ቦታ በቅርብ ርቀት ላይ ነው፡፡ መልዕክት እልክባቸውና የሚቀበልሽን ሰው ያዘጋጁልሻል"

"ምን ብዬ እንደማመሰግንዎት አላውቅም"

"በምስጋና ሳይሆን በተግባር እንደምትክሽኝ እምነቱ ነው፡፡ የልፋትሽ ውጤት ሀገርንና ወገንን ከሰይጣን ሴራ የሚታደግ በመሆኑ ለእኔ ከዚህ በላይ ትልቅ ምስጋና የለም"

"አይጠራጠሩ ፕሮፌሰር፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ትልቅ ስራ እሰራለሁ ብዬ አምናለሁ"

"ቀን ስትወስኚ ንገሪኝ"

"እሺ ፕሮፌሰር"

***

አባ ንቡረዕድ ተክለሀይማኖት ከወራት በፊት በስራ አጋጣሚ አግኝተውት ከነበረ ቄስ ጋር ያደረጉትን አጭር ውይይት ባስታወሱ ቁጥር ፀፀት እንደመርፌ ይወጋቸው ጀምሯል፡፡ እንዲያ አይነት ውይይት ማድረግ

በርካታ እጆች ታዩ:: ለአንደኛው ተሳታፊ እድል ተሰጠው:: ራሱን አስተዋውቆ ጥያቄውን አስከተለ::

"ጂም ማክዶናልድ እባላለሁ:: የአሜሪካውን የምስጢር ማህበር ስክል ኤንድ ቦንስ ወክዬ ነው የተገኘሁት:: ለጌታችን ለሉሲፈር ምንም እንደማይሳነው ባምንም ህዝቡን ለማሳመን እና በአምንታዊ መልኩ ቴክኖሎጂውን ተቀብሎ ጥቅም ላይ እንዲያውል ታዋቂ ባለስልጣናት ተጽእኖ ሊያሳድሩበት ይገባል የሚል የግል አቋም አለኝ:: ለጊዜውም ቢሆን ከማይታየው ጌታችን ሉሲፈር ይልቅ ህዝቡ ለሚገዙት ምድራዊ ባለስልጣናት እና የሀገር መሪዎች ቅርብ ነው:: ከእነዚህ መሪዎች ጋር ያለን ቅርበት እንዲሁም የሥራ ግንኙነት ምን ይመስላል? አመሰግናለሁ"

ማርዩ ኖኤል ፕሪስኮት መልስ ሰጠ::

"ጥሩ ጥያቄ ነው:: ጌታችን ማርዱክ ራ ይህንን እውነት ቀድሞ ስለተገነዘበ የእራሱ ከሆኑ የምድር ባለስልጣናት እና የሀገር መሪዎች ጋር ጥብቅ የሆነ ወዳጅነት እንዲሁም የሥራ ግንኙነት መስርቷል:: እነሱ ትዕዛዙን ያስፈፅሙለታል፤ እሱ ደግሞ ዝና፣ ክብር እና ሀብትን ይሰጣቸዋል:: ጊዜ ላለመሻማት ከእነዚህ ባለስልጣናት እና መሪዎች መሃል ሁለቱን ብቻ አስተዋውቃችኋለሁ::

"አንደኛው በአሁኑ ሰዓት ዓለምን በበላይነት የምትመራው አሜሪካ ውድ ልጅ የሆነው ዘቢግዋን ግርዚንስኪ ነው:: በአሜሪካ ህዝብ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ህይወት መሻሻል ላይ ጉልህ አስተዋጽኦ አበርክቷል:: የቀድሞውን የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ጨምሮ ያሁኖቹንም በማማከር ያገለግላል:: በርካታ መጻህፍቱን የሚቃወሙ ቢኖሩም እንደ እምነት መዕሐፍ ከእጃቸው የማይለዩዋቸውም በርካቶች ናቸው::

"ይህን ሰው አለቃችን ማርዱክ ራ ሉሲፈር አቀላምጦ ሲጠራው «ዘቢግ» እያለ ነው:: ታላቅነቱን ለመግለጽ:: በቴክኖሎጂ እና በኢኮኖሚው ዘርፍ እጅና ጓንት ሆነው እንደሚሰሩ አውቃለሁ:: ማርዱክ ራ ያስቸገሩትን እና አምላክነቱን ለመቀበል እምቢ ያሉ ሀገራትን መቅጣት ሲፈልግ ትዕዛዝ



የሚያስተላልፈው ለ«ዘቢግ» ነው:: የአንድን ሀገር ኢኮኖሚ በቀናት ውስጥ ማንኮታኮት ለ«ዘቢግ» የጨዋታ ያህል ነው:: ብራዚልን ጨምሮ ሌሎች ሀገራትን ያስታውሷል"

ወደ ቀጣዩ የሀገር መሪ ተሸጋገረ::

"ምንም እንኳን ስልጣኑን ለሌላ ቢያስተላልፍም የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ጆርጅ ኤፍ. ክሊንተንም የጌታችን የንግድ አጋር ነው:: በታዛዥነቱ በስሙ ለከፈተው ጆርጅ ኤፍ. ክሊንተን ግሎባል ኢንሼቲቭ ሁለት መቶ ሚሊዮን ዶላር ተበርክቶለታል:: እነዚህን ከመሳሰሉ ሰዎች ጋር ስለምንሰራ በታዋቂ ሰዎች አማካይነት ተፅእኖ የማሳደሩ ነገር ሊያሳስባችሁ አይገባም" አለና ትክዝ አለ::

"ይልቅስ ሊያሳስባችሁ የሚገባው ይህን ሁሉ ምስጢር ደርሳበት ይሆናል ብለን የምንጠረጥራት ኢትዮጵያዊት ደራሲ ሦስና አለማየሁ ረቂቅ ነው"

ስሜታቸው በ«ሦስተኛው ነብይ» ንግግር ተነሳስቶ ማበጥ ጀምረው የነበሩት ተሳታፊዎች ሚስማር እንዳገኘው ጎማ ሲተነፍሱ ታወቃቸው::

የሰፈረበትን ረቂት በአደራ ሲያስረክባቸው "ባለቤቷ እስክትመጣ የማይከፈት ብቻ ሳይሆን በጥንቃቄ የሚጠበቅ" በማለት ነበር። ይህችን ሴት እስኪያዩ ጉጉትም ፍርሃትም አደረባቸው። ምን አይነት ሴት ትሆን? ባልጠፋ ጽሁፍ ምስጢራዊ ረቂት ማዘጋጀቱን ለምን ፈለገችው?

ፕሮፌሰሩ ዝርዝር ውስጥ መግባት ስላልፈለገ በደፈናው "ለሀገር የሚበጅ ወሳኝ ስራ ልትሰራ ነው የምትመጣው። እርሶም ያግዟታል። ለስራው ትክክለኛ ስፍራው ይህ እንደሆነና ትክክለኛውም ሰው እርሶ እንደሆኑ ያሳመንኳት እኔ ነኝ" አላቸው።

"ትክክለኛ ስፍራው ኢቲሳ እንደሆነ፣ ትክክለኛው ሰውም እኔ እንደሆንኩ በምን አወቅህ?"

"ቆይተው ይረዱታል። የልጅዎን ያህል እንደሚያቀርቧት እርግጠኛ ነኝ"

አባ ፕሮፌሰሩን ያምኑታል። ንግግሩ በመጠኑ አረጋጋቸው። "መቼም ለክፉ ነገር አሳልፎ አይሰጣቸውም። ግን... የምትሰራው ስራ ምን ይሆን? እኔስ የማግዛት ምን ይሆን? የምትመጣበት ቁርጥ ቀን መቼ ይሆን? ምን ያህል ጊዜ ትቆይ ይሆን? ምን ትበላ፣ ምንስ ላይ ትተኛ ይሆን? ከሠለጠነ ሀገር ለመጣች እንስት የገጠር ደብር መኝታና ምግብ.... ፕሮፌሰሩን ካሰናበቱት እለት አንስቶ አእምሯቸውን በተለያዩ ጥያቄዎች አጨናንቀው ሰነበቱ።

# -8-

## ስትሬሳ፣ ጣሊያን

"ዛሬ አስቸኳይ ስብሰባ የጠራሁበት ምክንያት...." አለ ማርዮ ኖኤል ፕሪስኮት እንግዶቹን እየተመለከተ። "ረቂቁ የተደበቀበት ስፍራ ተገኝቷል የሚለውን የምስራች ለማብሰር ነው" አላስጨረሱትም። አዳራሹን በጩኸት አናጉት።

"እልልል...!"

"ከጌታችን ሉሲፈር እይታ ተደብቆ የሚቀር ነገር የለም!"

"ወደስፍራው ሰው ይላክ!"

"ረቂቁ ተፈልጎ ይምጣና በጉባዔው አባላት ፊት ይቃጠል!"

"ደራሲዋም፣ ኢትዮጵያም ከቁጥጥራችን ውጭ አይሆኑም!"

"ቅድስት የተባለችውን ሀገር ህዝብ በጌታችን በሉሲፈር ዙፋን ስር እናንበረክከዋለን!"

"እንዴ ተረጋጉ!" ሲል ጮኸ ማርዮ ፕሪስኮት። ረዥም ደቂቃ እጁን ሰቅሎ ቢቆይም ትዕዛዙን ተቀብለው ዝም ባለማለታቸው ተበሳጭቷል።

"ተረጋጉ ስትባሉ ተረጋጉ። እንደምታስቡት ቀላል አይደለም። ቅድስት የተባለችውን ሀገር ህዝብ በጌታችን በሉሲፈር ዙፋን ስር እናንበረክከዋለን ስትል የጮህከው ማክዶናልድ እየገመጡ የወሲብ ፊልም የመመልከትን

ያህል ቀላል አይደለም!"

ሌሎቹ ሲስቁ እና ሲንሾካሾኩ ጮሆ የተናገረው ግለሰብ በአፍረት ፊቱ ካሮት መስሎ አንገቱን አቀረቀረ። ከስኮትላንድ የሰይጣን ወንድማማችነት ማህበር ተወክሎ የመጣ ልጅ እግር ተሳታፊ ነው። በማክዶናልድ በርገር እና በወሲብ ፍቅሩ ይታወቃል። የኒው ኦርሊየንስ ፖሊስ በወሲብ ቅሌት የተነሳ ሦስት ጊዜ አስሮ ፈቶታል።

"ያንን ህዝብም ሆነ ሀገሪቱን የጌታችን የሉሲፈር ተገዥ ለማድረግ ከምታስቡት በላይ ፈተና ይጠብቀናል። እምነቱ ዋስትና እና ከለላ ሆኖት የሚኖር ህዝብ ነው። በሌሎች ላይ የተቀናጀውን ድል በኢትዮጵያና በህዝቧ ላይ መቀዳጀት ያለመቻላችን ማርዱክ ራ ሉሲፈርን ሁሌም እንዳሳሰበው ነው። በአንጻራዊ መልኩ ግብረሰዶምን ብናስፋፋም፣ የእምነት ልዩነት ፈጥረን ብናጣላም፣ በርሀብ እና በችግር ልንቀጣው ብንሞክርም ህዝቡ ወይ ፍንክች። አምላኬ ብሎ የሚያምንበትን እግዚአብሔር፣ አማላጅ ብሎ የሚተማመንባትን ኪዳነምህረት ሙጥኝ ብሎ ሲያቃጥለን ይኖራል።

"ያም ሆኖ ተስፋ አንቆርጥም። ውጤት እስክናገኝ ድረስ እንታገላለን። ረቂቁ የተደበቀበት ስፍራ ፍንጭ መገኘቱ ቀላል ውጤት አይደለም። ሳናገኘው ቀርቶ ታትሞ ለህዝብ ቢደርስስ? ጉዳችን ይፈላል። እንደዚህ ከሆነ ደግሞ እንኳንስ ህዝቡን በማርዱክ ራ ሉሲፈር ዙፋን ስር ልናንበረክከው ሌላውም አለም ያምፅብናል። ረቂቁ ይህን ያህል ተጽእኖ የመፍጠር ሀይል እንዳለው እወቁ። ለዚህም ነው ሳናገኘው እንቅልፍ አይኖረንም የምንለው?"

የተሳቀበትን ጀብደኛ የወሲብ አርበኛ በብስጭት ተመለከተው። ሲሰርቅ እንደተያዘ ሌባ ዳግመኛ አቀረቀረ። በመሃል አንድ እጅ ለጥያቄ ተቀሰረ። የሉቺዮ ጂሊኮልሸንባች ነበር። እድሉ ተሰጠው። ማርዮ ኖኤል ከሌሎቹ ይልቅ እሱ ላይ እምነት አለው።

"ለመጀመሪያ መፅሐፏ ግብዓት የሆናትን መረጃ ማን እንደሰጣት ያለማወቁ ሲከነክነኝ አለ። የዚህኛውንስ መረጃ ከየት አገኘችው? ከታማኝ ምንጭ ባታገኝ የጌታችንን እቅድም፣ ማክሸፊያ ዘዴም በረቂቅ መልክ



አዘጋጅታ ባላስተመጠች። ምስጢራችንን ሁሉ ማን ነገራት?" ማርዮ ኖኤል ፐሪስኮት አጭር ምላሽ ሰጠ።

"የቀድሞ አባላችን ካርሎ ዛጋሚ እንደሆነ ያወቅነው በቅርብ ነው!"

ከሁሉም አንደበት ተመሳሳይ ቃል ተሰማ።

"እርፍ!"

ወሳኝ የሆኑ ምሥጢሮች እና መረጃዎች ሰስና እጅ ለመግባታቸው እርግጠኞች ነበሩ። በ33ኛ ዲግሪ (እርከን) ላይ ያለ አባል የማያውቀው ምስጢር የለምና።

# -9-

## ፓልማ፣ ማሎርካ

የቀድሞው የኢሉሚናቲ ከፍተኛ ባለስልጣን የሚሰጠውን ጋዜጣዊ መግለጫ ለመከታተል በርካታ ጋዜጠኞች ከሰዓቱ ቀደም ብለው በስፍራው ተገኝተዋል። የመግለጫው ርዕሥ ነበር ቀደም ብለው ቦታቸውን እንዲይዙ ያስገደዳቸው።

**"ሠይጣንን አግኝቼ እንዳነጋገርኩት እና ሀሳቡን እንደተረዳሁት"**

ሰይጣንን አግኝቶ ያነጋገረን ሰው መልሶ ለማነጋገር እና የሚለውን ለመስማት የቋመጡት ጋዜጠኞች አዳራሹን አጨናንቀውት ሳለ በጉጉት የሚጠበቀው ካርሎ ዛጋሚ መድረኩ ላይ ተከሰተ። የጋለ ጭብጨባ ተቀበለው። ከአንገቱ ጎንበስ ብሎ አጸፋታውን ከመለሰ በኋላ በቀጥታ ወደ መግለጫው አመራ። የመግለጫው አጠቃላይ ሀሳብ ቀደም ብሎ በወረቀት የደረሳቸው ጋዜጠኞች ዝርዝሩን ለማዳመጥ ራሳቸውን አዘጋጁ።

"ይህን ጋዜጣዊ መግለጫ ያለምክንያት አላዘጋጀሁም። የሰይጣንን ሴራ በእናንተ አማካይነት ህዝብ ዘንድ ለማድረስና ለማንቃት ነው። ህዝብ ከነቃ፣ አይኑን ከከፈተና እውነቱን ከተረዳ ለሰይጣን ሴራ አይረታም የሚል እምነት አለኝ። የኢሉሚናቲ 33ኛ ደረጃ አባል በነበርኩበት ጊዜ በተደጋጋሚ ከሰይጣን ጋር ተገናኝተን ተወያይተናል። ሀሳቡን ነግሮኛል። ፍላጎቱን ዘርዝሮልኛል። በደንብ ለመወያየትና ሀሳብ ለማንሸራሸር መግለጫውን በቃለምልልስ መልክ ብናካሂደውስ?"

ቤቱ በመስማማቱ ጥያቄና መልሱ ተጀመረ። ከተለያዩ አቅጣጫዎች



ጥያቄዎች ጎረፉ።

**"እውነት ሰይጣንን አግኝተው አነጋግረውታል?"**

"እኔ ብቻ ሳልሆን በምሥጢር ማህበራቱ ውስጥ የበቃ ሊቅነት (የማስተርነት ደረጃ) ያለን፣ ሁነኛውን ቦታ የተቆጣጠርነው ሁሉ ከሰይጣን ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ስላለን እናገኘዋለን፣ እናወራዋለንም። ይህ ብዙ ሊያስደንቀን አይገባም። በተለይ እኔና የተወሰንን ወንድሞች (የማስተርነት ደረጃ የደረስነው) የአንቶን ዛንዶርሌቪን «ዘሳታኒክ ባይብል» እና «ዘዴቭልስ ኖት ቡክ» በጥልቀት እናነብ ስለነበር በተደጋጋሚ ተገናኝተን ሀሳብ ተለዋውጠናል"

ወጣት ጋዜጠኛ ፍርሃቷ በግልጽ እያስታወቀ፣ "በእየሱስ ስም!" አለች። የሰሚት ሳቁባት።

**"ለመጀመሪያ ጊዜ ከሰይጣን ጋር ፊት ለፊት ሲገናኙ ምን ተሰማዎ?"**

"አልዋሽም። በጣም ነበር የደነገጥኩት። እሱም ለመጀመሪያ ጊዜ እንዳገኘኝ እንደምትመጣ አውቅ ነበር ነው ያለኝ። የማይለመድ የለምና እየለመድኩት ስመጣ ተረጋጋሁ"

**"በምስጢር ማህበራቱ ውስጥ ያላችሁ መሪዎች ከሰይጣን ጋር ፊት ለፊት መገናኘቱን ለምን ፈለጋችሁት?"**

"ዓለምን በቁጥጥር ስር ለማዋል የሚያስችለንን ሃይል እንዲሰጠን። ካመንክበት ይሰጥሃል"

**"ሰይጣን መጥፎ መንፈስ መሆኑን እያወቃችሁ እንዴት አመናችሁት? ማመንም ብቻ ሳይሆን ተገዛችሁለት?"** ሦስና ነበረች።

"የምስጢር ማህበር አባል ስትሆኝ መልካምነቱ እንጂ ክፉነቱ፣ ብርሃንነቱ እንጂ ጨለማነቱ አይታይሽም። ሰይጣን ልክ እንደ እግዚአብሔር መመስገን፣ መመለክ፣ መወደስ ስለሚፈልግ ላመሰገኑት፣ ላመለኩትና ላወደሱት የሚፈልጉትን ይሰጣቸዋል። የምንፈልገውን ስለሚሰጠን ነው

የተገዛንለት"

**"ለሰይጣን ተገዝቻሁለት እና የፈለጋችሁትን ሰጣችሁ። ምን ይጠቀማል?"**

"እግዚአብሔር እንደሚያዝን ያውቃልና ይደሰታል። ይህ ለእሱ ትልቅ ጥቅም ነው። እግዚአብሔርን እንደማሳዘን የሚያስደስተው ነገር የለም። በሌላ በኩልም የሚያመልከውን ያገኛል። በሚያመልኩት አማካይነት አለምን ያምሳል፣ ያበጣብጣል፣ ጦርነት እንዲነሳና የሰዎች ደም እንዲፈስ ያደርጋል። የሰው ልጆች ተበጣብጠው ማየት ትልቅ ፍላጎቱ ስለሆነ ይህ ለእሱ ሁልጊዜም የሚረካበት እና የሚደሰትበት ጥቅሙ ነው"

**"ሰዎችን የሚቆጣጠረው በምን አይነት መንገድ ነው?"**

"ብዙ ዘዴዎች አሉት። ዋናው ግን በደካማ ጎናቸው መግባት ነው። ለብልጭልጭ እና ለዓለማዊ ነገሮች ፍላጎት እንዳላቸው ስለሚያውቅ በዚያ በኩል ነው የሚመጣባቸው። ልብ ብላችሁ ካስተዋላችሁ ሰዎች ለዓለማዊ ነገር ያላቸው ፍላጎት እየጨመረ ነው። ያንን ለማግኘትም የማያደርጉት ነገር የለም። የሚፈልገው ይህንን ነው። ሌላው የሰዎችን አእምሮ የሚቆጣጠርበት ዘዴው ማፍዘዝ እና ማደንዘዝ (ሃይፐኖቲዝም) ነው። የፈዘዘ እና የደነዘዘ አእምሮ ተራ ነገሮችን ለመቀበል ፈጣን ነው። ሰይጣን እጅግ ጥንታዊ የሆኑ ውሸቶችን ስለሚያውቃቸው እንደእኛ ለተከተሉት ሁሉ በሚያሳምን መንገድ ይነግራቸዋል። ከጥንት ጀምሮ በመኖሩ እና የተከሰቱትን ነገሮች ስለሚያውቃቸው በሚያሳምን መልኩ ሲነግረን እናምነዋለን። በእነዚህና መሰል ነገሮች የሰዎችን አእምሮ በቀላሉ መቆጣጠር አይሳነውም።"

**"ሠይጣን ይበልጥ ትኩረት ያደረገባቸው ሀገራት ይኖሩ ይሆን?"**

"ኢትዮጵያና ሩሲያ" ሶስና ደነገጠች።

**"ለምን መረጣቸው?"**

"የእምነታቸውን ጽናት ስለሚያውቅ"

**"ዋና አላማውን ዳግም ጠቅለል አድርገው ቢያስረዱን?"**



"ሰዎች በእግዚአብሔር ላይ ያላቸው እምነት እንዲጠፋና ፈጣሪ የለም ብለው እንዲያምኑ ማድረግ። ይህን ለማድረግ የሚጠቀምባቸውን ዘዴዎች በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች መመደብ እንችላለን። አንደኛው ሰይጣንም እግዚአብሔርም የሉም የሚለውን እምነት እንዲቀበሉ በማድረግ በእሱ የሀሰት ያለመኖር የእግዚአብሔርን ያለመኖር ማሳመን። ሁለተኛው አእምሯቸውን በማፍዘዝ መቆጣጠር፣ ሦስተኛው መፅሐፍ ቅዱስን በተዛባ እና በተሳሳተ ትርጉም እሱ በሚፈልገው መንገድ እንዲረዱ ማድረግ። ሦስተኛውን ዘዴ እሱ ራሱ «መፅሐፍ ቅዱስን በእሳት ሳያቃጥሉ ማጥፋት» ነው የሚለው።"

ቀደም ብላ «በኢየሱስ ስም!» ያለችው ልጅ አሁንም «በኢየሱስ ስም!» ብላ አማተበች።

**"አሁን ደግሞ ስለተባባሪዎቹ ይንገሩን?"**

"የምስጢር ማህበራቱን ዋነኛ አባላት ጨምሮ በርካታ የዓለም ህዝብ ተገዥው ነው። ሰዎች ከረዥም ጊዜ ጀምሮ ለምድራዊ ሽልማቶች ሲሉ ከሰይጣን መንፈስ (jinn) ጋር ሲሰሩ ኖረዋል። አሁንም እየሰሩ ነው። በቅርብ የማውቀውን እውነት ልንገራችሁ። ስለቻርልስ ዳርዊን የአዝጋሚ ለውጥ ንድፍ ሀሳብ (ቲዮሪ ኦፍ ኢቮሊሽን) ታውቃላችሁ። ዳርዊን የሰው ዘር በአዝጋሚ ለውጥ ከዝንጀሮነት ወደ ሰውነት እንደተለወጠ ነው የሚናገረው። ሰው የፈጣሪ ፍጡር እንደሆነ ዳርዊንም ሰይጣንም ያውቃሉ። ነገር ግን ሰዎችን ለማሳሳትና ፈጣሪ የለም ለማለት ሰይጣን ዳርዊንን ተጠቀመበት። ይህን ንድፈ ሀሳብ ለዳርዊን በግል ያስተማረው ሰይጣን ነው"

ቤቱ በሳቅ ተናጋ። "አትሳቁ። እውነቱን ነው ሰይጣን ነው ያስተማረው"

ሌላ ሳቅ።

**"ሰይጣን ራሱን እንዴት ነው የሚያየው?"**

ብዙዎች በጥያቄው ግር ተሰኝተው አጉረመረሙ። ካርሎ ዛምቢ ግን ጥያቄውን አድንቆ መልስ መስጠቱን ቀጠለ።

"ጥሩ ጥያቄ ነው። አመጣጥህ ገብቶኛል። ራሱን በእርቀት የሚገኝ ፕላኔት ነዋሪ አድርጎ ነው የሚያየው"

"የጋራ ውይይታችሁ ርዕስ በአብዛኛው በምን ላይ የሚያጠነጥን ነው?" ዳንኤል ኢስቱሊን ነበር።

"በእሱ ኃያልነት፣ በፈጣሪ ያለመኖር እና በምድራዊ ሀብት፣ ዝና እንዲሁም ስልጣን ዙሪያ። እኛ ለእሱ ኃያልነት እንተጋለን፣ የፈጣሪ ያለመኖርን እንሰብካለን። እሱ ደግሞ የፈለግነውን ምድራዊ ሀብት፣ ዝና እና ስልጣን ይሰጠናል። በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ስምምነት ነው።

"በሰይጣን ውስጥ ያሉትን መንፈሶች እንዲህ ናቸው ብለን ልንገልፃቸው እንችላለን?" ሦስና ለሁለተኛ ጊዜ ጠየቀች።

"አዎ! የሰይጣን መንፈሶች ‹‹ጂኒ›› ይባላሉ። ደረጃ አላቸው። ምድር አካባቢ ያሉት የሀይለኝነት ሁኔታ አይታይባቸውም። ከምድር ወደ ሰማይ ከፍታ በጨመርን ቁጥር ነው ከሀይለኞቹ እና ረቂቆቹ ጂኒዎች ጋር የምንገናኘው። የሁሉም የጋራ አጀንዳ እና ፍላጎት እግዚአብሔር የለም የሚለው እምነት በሰው ልጆች ልቦና ውስጥ ሰፍኖ ማየት ነው። ስለዚህ በፈጠራችሁ ይሁን የሰይጣንን ረቂቅ ሴራ ህዝብ ዘንድ አድርሱና አከሽፉበት። የጋዜጣዊ መግለጫው ዋና አላማም ይህ ነው"

ጋዜጠኞቹ ለካርሎ ዛጋሚ ጥያቄ አምንታዊ ምላሽ ቢሰጡም የመጨረሻ ጥያቄ መጠየቃቸው አልቀረም።

"ሰይጣን ተጨማሪ አሳሳች ዘዴ አለው?"

"እንዴታ! በሉሌዎቹ አማካይነት የሚጠቀምበት ዘዴ አለው። ፊልምና ሙዚቃ። ሉሌዎቹ የመዝናኛውንኢንዱስትሪ ስለተቆጣጠሩ ችግር የለባቸውም። ቢዱቭል አድቮኬት ላይ አልፓቺኖ የሰይጣንን ሚና ነው የሚጫወተው። ኬኑ ሪቪስም ቢሆን በአንዱ የፊልም ትዕይንት ላይ የምስጢር ማህበራቱ መገለጫ በሆነው ሰንጠረዥማ ወለል ላይ ቆሞ እንመለከተዋለን። ሆን ተብሎ የተደረገ ነው። ሰንጠረዥማ ወለል አሉታዊ

ኃይልን የሚያስተናግድ የሰይጣን ወለል ነው። የናሽናል ትሬዠር ፊልም እውነትም ከዚህ የሚርቅ አይደለም። በፊልሙ ላይ ቅርሱን (ሀብቱን) የሚያገኙት ሰዎች በሰለሞን ቤተ መቅደስ የግል ክፍል ውስጥ ያገኙት ሀብት ወርቅ እና የከበረ ድንጋይ አይደለም። ለሰይጣን የሚሰገድበትን መንገድ የሚያሳይ ምስጢራዊ መፅሐፍ ነው። በአስማት የተሞላ መፅሐፍ። እና የተከበራችሁ ጋዜጠኞች ከዓለም ህዝብ የተደበቀውን እውነት ይፋ እንደምታወጡት እና ሰይጣንን እንደምታሳፍሩት እምነቴ ነው"

መግለጫው አበቃ።

# -10-

## ስትሬሳ፣ ጣሊያን

ዛሬም ንዴት ውስጡን እያቃጠለው ነው። በተራ ክስ የተነጠቀው ስልጣኑ የህልውናው መሰረት ነበር። የተደበቀውን ምስጢር፣ ወደከፍተኛ የኃይል ሙላት የሚያሸጋግረውን ምስጢር የሚያጠናበት እና የሚያውቅበት ስልጣን። ዛሬ ወደ ተራ አባልነት ወርዷልና የተደበቀውን ምስጢር የሚያጠናበት እድል እና አጋጣሚ አይኖረውም። የተደበቀውን ምስጢር በማይታዩ ጌቶቻቸው አማካይነት የሚያጠኑት በከፍተኛ የሥልጣን ደረጃ ላይ ያሉትና የተፈቀደላቸው ብቻ ናቸው። ከተፈቀደላቸው መዝገብ ላይ ተሰርዟል። እድሜ ለፓብሎ ሪቬራ።

"ሰው ካወቀበት አምላክ ነው" የሚል መርዝ ትምህርት አስተምሯል ብሎ ከሰሰው።

"የጌታችንን የማርዱክ ራ ቦታ የምትመኝ አንተ ማነህ?" ሲሉ በከፍተኛ ማስጠንቀቂያ ማዕረጉን ገፈው ተራ አባል አደረጉት። ለእሱ ሞት እና በቃላት የማይገልፁት ውርደት ነበር።

...እድሜ ለፓብሎ ሪቬራ።

ለአልቤርቶ ሪቬራ ሀያል እና ላፍለ ልእለ ሰብ ከመሆን የተሻለ የመጨረሻ ምርጥ ነገር የለም። ጥቂት ሲቀረው ነው ከመንገዱ የመለሱት። የኃያልነት ጫፍ እንደሚደርስ፣ የምስጢሩን የመጨረሻ ጠርዝ እንደሚነካ በዚህም ያለማንም እርዳታና ድጋፍ አምላክነቱን እንደሚያውጅ እርግጠኛ



ነበር። ዛሬ ከተራነቱ ጋር አብሮ አለ።

ድቁናውን የተቀበለው የ11 ዓመት ልጅ ሳለ ቢሆንም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የፍሪሜሰንስ አባሉ ማንሊ. ፒ. ሆል አድናቂና ተከታይ ነበር። በአንዳንድ ሀሳቦች ላይ ልዩነት ቢኖረውም።

ለንባብ የሚጠቀምበት ክፍሉ ውስጥ ነበር። ሰፊ እና እጅግ የሚያምር ክፍል። መደርደሪያውን ከሞሉት መጻህፍት በብዛት የሚታዩት የማንሊ. ፒ.ሆል እና የአልበርት ፓይክ ናቸው። ከፒ. ሆል መጻህፍት መካከል ሦስት ያህሉን ከመደርደሪያው አንስቶ ጠረጴዛው ላይ አስቀመጣቸው።

"ዓለምን ያነጋገሩ ብቻ ሳይሆኑ ያናወጡ" አለ በውስጡ።

ብላክ ማጂክ፣ ዘ ሎስት ኪይስ ኦፍ ፍሪሜሰነሪ፣ ዘ ሴክሬት ቲቺንግ ኦፍ ኦል ኤጅስ

በየተራ የሚያውቃቸውን ገጾች ከፈተና የሚሰቡትን ዓረፍተ ነገሮች አነበበ።

"...የሰው ልጅ በእራሱ ፍላጎት የሚከውነው አንድም ነገር የለም። በዙሪያው የሚከወኑት ነገሮች የማይታዩ ፍጡሮች ተግባራት ውጤቶች ናቸው። ዙሪያችንን የከበበን የማይታይ ዓለም አለ። ብዙ ሰዎች ስለማይታየው ዓለም ምንም አይነት እውቀትና ግንዛቤ የላቸውም። ይህን የስነ-ፍጥረት እውነት ጠንቅቀው የሚያውቁት የጥንቆላውና የአስማቱ ጥበብ የገባቸው፣ ምስጢራዊው እውቀት የተገለፀላቸው ብቻ ናቸው"

"ልክ እንደእኔ" አለ አልቤርቶ ሪቬራ። "ጥበቡ እየገባኝ፣ ምስጢራዊው እውቀት እየተገለፀልኝ ነበር። እድሜ ለዚያ እንከፍ ከእውቀት መንገዴ አሰናከለኝ"

ዳግም ወደንባቡ ተመለሠ።

"በዙሪያችን የከበበንን አለም አናየውም። አንዳስሰውም። አናሸተውም። አናዳምጠውም። ያም ሆኖ ተፅእኖውን አሳርፎብናል። ይህ ዓለም የመንፈስ

ዓለም ብለን የምንጠራው ነው። መለኮታዊ ዓለም ብለው የሚጠሩትም አሉ። እጣ ፈንታችን እና እድላችንን የሚወስንልን ይህ የማይታይ ዓለም ነው'

"ይህን ስለማምን እኮ ነው ይህን መንፈሳዊ ድብቅ ዓለም ሳጠናው የኖርኩት" ፒ ሆል «የመንፈሥ ዓለም» ብሎ የሚጠራው ዓለም የአልቤርቶ ሪቬራ ያላለቀ ጥናት ነው። እጣ ፈንታውንና እድሉን የሚወስንለትን የማይታይ ዓለም ከማጥናት የሚያግደው ሞቱ ብቻ ነው። እድሉ እና እጣፈንታው የተሻለ የከፍታ ስፍራ ላይ ያስቀምጠው ዘንድ እጥብቆ ይመኛል።

"የሰው ልጅ ካወቀበት አምላክ ነው"

የንባብ ክፍሉን መስኮት እስከመጨረሻው ከፍቶ ንጹህ አየር በጥልቀት ከሳበ በኂላ ወደንባቡ ተመለሰ።

"የሰው ልጅ ከማይታየው ዓለም ውጭ ምንም አይደለም። በአራሱ የሚፈጽመው ነገር የለም። የማይታየውን ዓለም የወረሩ እንግዳ ፍጡሮች በዙሪያችን ይኖራሉ። የጋኔል መንፈስና መላዕክት ብለን የምንጠራቸው ናቸው። ባናያቸውም በህይወታችን ውስጥ አይነተኛውን ሚና ይጫወታሉ። እጣፈንታችንን የሚወስኑልን እነዚህ ፍጡራን ናቸው። የማይታዩት መጥፎ ፍጡራን በላቲን ቋንቋ «ኢንኩቡሥ» እና «ሲኩቡስ» ተብለው ይጠራሉ። ወደእንግሊዝኛ ስንተረጉመው «Mare» የሚለውን ስያሜ ያገኛል። ወንድና ሴት ጥገኛ ህዋሳት ማለት ነው። በቤተክርስትያን አባቶቹ ቅዱስ አውግሥቲን እና ቅዱስ ቶማስ ገለፃ መሰረት ኢንኩቡስ እና ሲኩቡስ ሰዎችን በመኝታ ሰዓት የሚበጠብጡ ርኩሳን መናፍስት ናቸው"

"በዚህ አልስማማም" አለ በመስኮት ወደውጭ እየተመለከተ። "የሚበጠብጡ ርኩሳን መናፍስት ሳይሆኑ የሰው ልጅ በእንቅልፍ ሳይዘናጋ ተግቶ የተደበቀውን ምስጢራዊ እውቀት እንዲፈትሽ ከማይታየው አለም ግዛት አስተዳደር የተላኩ የእውቀት ወደ ዘማቾች ናቸው"

ወደቁም መስታወቱ ተጠጋና ከወገቡ በላይ ያለውን ልብስ አወለቀ። ንቅሳቱ ደምቆ ታየው። በግራ ደረቱ ላይ ሲኩቡስ በቀኙ ላይ ደግሞ



ኢንኩቡስ የሚሉ ፊደላት በላቲን ቋንቋ ተነቅሰዋል። ፈገግ አለ። እጣፈንታውን እና እድሉን የሚወስኑለት የማይታየው ዓለም የእውቀት ወደ ዘማቾች ናቸውና ባያያቸውም እያከበራቸው ይኖራል። ዛሬ በዚያ እንከፍ ጦስ ከመንገዱ ቢሰናከልም በእነሱ እርዳታ የተደበቀውን ምስጢራዊ እውቀት ለማግኘት የማይፈነቅለው ድንጋይ አይኖርም። ታላቁን ስልጣኑንና ስልጣኑ እንዲያውቅ የሚፈቅድለትን ምስጢራዊ እውቀት ያሳጣውን ቁጥር አንድ ጠላቱን ግን ሳይበቀል እንቅልፍ አይኖረውም። ያውም እስከተባባሪዎቹ።

# -11-

## አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

እስረኛውን ቄስ ከቀን ቅዥት ያባነነው በር ላይ የቆመው ጠባቂ ጥሪ ነበር። እዚህ አካባቢ ትልቅ ትንሹ ታዛዥ ነው። የገንዘብን ሃይል ቀደም ብሎ የተገነዘበ ቢሆንም እዚህ አካባቢ ለሚኖረው ጉልበት እርግጠኛ አልነበረም። አሁን ገንዘብ የትም ስፍራ ጉልበት እንዳለው አረጋግጧል። ያም ሆኖ የተወሰኑ ጠሳቶችን እንዲሁም የሚንቁትን ሰዎች አላጣም።

"መልዕክት አለህ" አለው ፖሊሡ ግራና ቀኙን በስጋት እየተመለከተ። ድምጹን በጣም ቀንሶ ነበር የሚያወራው። የቄሱን ጠቀም ያለ ጉርሻ የለመደ ጥቅመኛ ነው። ቁራጩን ወረቀት አስረከቦት ወደምድብ ስፍራው ተመለሰ። ቄሱ ወረቀቷን እየገለጠ ወደከፍሉ ተመለሰ።

"እምሳያህን ስለተካህልን እናመሰግናለን። ስለቀሪው ነገር አታስብ"

በቃ መልዕክቱ ይሄው ነበር። ድፍን ያለ።

ምን ማለታቸው ነው? ሲል እራሱን ጠየቀ። ስለቀሪው ነገር አታስብ!?

- ልጅህን እንቀባረን እንይዘዋለን?
- ረቂቁን አግኝተን እናቃጥለዋለን?
- በሀገርህ የጀመርነውን እቅድ እናሳካለን?
- የምትፈታበትን መንገድ እናመቻቻለን?

አልገባውም። ዓለማዊ ነገሮችን እንደሚፈልገው ሳያሳካ እስር ቤት



በመወርወሩ ቢበሳጭም ልጁን በመተካቱ ተጽናና። የህይወት መመሪያውን አስታወሰ «ተደስተህ ኑር! ተደስተህ ለመኖር የሚያስችሉህን ነገሮች ለማግኘትም አስፈላጊውን መስዋዕትነት ክፍል!» ይህን መመሪያውን ስልጁም ሲግተው ኖሯል። ልጁን ለቅጽበት አስታወሰው።

አልጋወራሽ ልጁ...! ሌላው ቀርቶ ወሲባዊ ቅብጥብጥነትን ሳይቀር ያወረሰው ልጁ...! የአባቱን ቃል እንደ እግዚአብሔር ቃል የሚያከብረው ልጁ።

ሀሳቡን ከልጁ ላይ መልሶ የእራሱን ህይወት በትዝታ ቃኙ፡ የወሲብ ገጠመኞቹን ጭምር። ፒያሳ....ካዛንቺስ....ሃያሁለት...ቦሌ....ከረን.... ቀስተ-ደመና...ሀረር ባር...ፍሉሪዳ....ኮንትኔንታል....ሰሜን ሆቴል...ወዘተ ያልተዝናናበት ቡና ቤት የለም። ህይወትህን ደስታ አትንፈጋት በሚለው መመሪያው ያላዳረሰው ሆቴል እና መቀነቷን ያላስፈታት! ቀሚሷን ያላስወለቃት ሴት የለችም። ደግነቱ እንደአንዳንድ አስዳቢዎች እስከክብር ልብሱ፣ ቆብና ቀሚሱ አይገባም። ዋና ዋናዎቹ ትውስታዎች ፊቱ ድቅን አሉ።

ኮንትኔንታል፦

የዚያን እለት ከጠይሟና ስትስቅ ከምታምረዋ ልጅ ጋር ነበር። ደጋግሞ አንሶላ ተጋፈታል። አዳር ሳይሆን ደርሶ መልስ... አጭር ቆይታ። ቢሞት ውጭ አያድርም። ከጣሙት ቀን ትልቅ ሆቴል ይቀጥራቸዋል እንጂ ሌሊቱን ሙሉ ጠረናቸውን እየማገ ማሳለፉ ምቾት አይሰጠውም። አስማታዊ ፈገግታዋን አስቀድማ "ጠፋህ?" አለችው። ጥመዋለች። ውልብ ሲለው ይጎበኛታል። የጠየቀችውን ስለሚከፍላት፣ ወሲብም ላይ ጎበዝ ስለሆነ መምጣቱን የምትጠባበቀው በጉጉት ነው።

"አልመች ብሎኝ" አላት እየሳቀ። የሚጠጣውን ተመለከተች። ጎርደን ጂን።

"ሲያምረኝ ብቻ ነው ጎርደን የምጠጣው" ያላትን አስታወሰች።

"ዛሬም ጎርደን?" እየተስለመለመች።

እያደመጥን ያደግነው

አውሮፕላን መጣ እየገሠገሠ
በዘፈን አንደኛ ጥላሁን ገሠሠ

የሚለውን ዘፈን ነበር:: አሁን ግን ዘፈኑ ተቀይሮ

የጥንቷን መኪና ይሿታል ታኖስ
በወሲብ አንደኛ አስመሳዩ ቂስ

የሚል ሆኗል::

እስረኛው ሁሉ ሆ ብሎ ሳቀ:: ክፍሉ በአንድ እግሩ ቆመ:: አስር እስረኛ እፍግፍግ አድርጎ የያዘ ክፍል ነው:: ቂሱ ክፍሉን ብቻ ሳይሆን ቃሊቲ የሚለውንም ቃል አምርሮ ጠላ:: ቃሊቲ የሚለውን ቃል ባሠበ ቁጥር እስር ቤት የሚለውን ቃል ያስታውሳል::

"እንዴ ችከላ ላይ አስተማማኝ ነች እንዴ?" ይላል አንዱ ወሬውን ማሟሟቅ ሲፈልግ:: ችከላ በእስረኛው ዘንድ ወሲብ የሚለውን ቃል ይወክላል::

"ኢዲያሚን ዳዳን አይተህ ማየት ነው:: ሁለት ሴት ይዞ አይደል የሚተኛውና የወሲብ ሻምፒዮን ነኝ እያለ ጉራውን የሚነዛው!? ይሄኛው የሀገራችን አልጋ ስፋት እየገደበው እንጂ ለሦስት እና አራት ሴት የሚሆን አቅም እና ጉልበት እንዳለው ታማኝ ምንጮች አረጋግጠዋል"

"ያን ኃይልና ጉልበት የኢሉሚናቲዎች አምላክ የሆነው ሰይጣን ሰጥቶት ይሆናል እንጂ ጤነኛ ሰው መቼም አራት ሴት በአንድ ጊዜ..' አሁንም እስረኛው ክፍሉን በሳቅ ያናጋል::

"ያላዳረሳት ሴት የለችም አሉ:: ይሄ ድግምት የማይሰራው አለ ብላችሁ ነው?"

"በህግ አምላክ!" ይላል ሁሉ ነገር ከአቅም በላይ ሲሆንበት::

"በህግ አምላክ! አልደረስኩባችሁም:: አትድረሱብኝ:: ስም በማጥፋት



ወንጀል እንደምከሳችሁ እወቁ"

"ምን ብለህ?" ይለዋል መስፍን እያላገጠ::

"ወሲበኛ ነው ብላችሁ ስሜን በማጥፋታችሁ......."

"ቅንዝራም!" እስረኛው ሁሉ በአንድ ድምጽ ይጮሀል::

"ልብ አድርጉ ተውኝ:: ከውጭ ኃይላት ጋር ያደመ ብላችሁም መልካም ስሜን...."

"ከሃዲ!" ሲል ይጮሃል እስረኛው በአንድ ድምጽ::

ይህ ማስፈራሪያ መንገድ አላዋጣ ሲለው ስልቱን ይቀይራል:: አፋቸውን እንደሚያሲዛቸው እርግጠኛ በመሆን::

"እያንዳንድሽ እምቢ ካልሽ ጢንዚዛ አድርጌ በመስኮት አበርሻለሁ"

"ምን?" ሲሉ ይጮሃሉ::

"ሲያሻኝ ጢንዚዛ አድርጌ፣ ሲያሻኝ አምበጣ... ሲያሻኝ ፌንጣ...." ይሄኔ ቤቱ ለሁለት ይከፈላል:: ግማሹ ይህ ድግምታም ቂስ ያለውን ለመፈጸም ሰይጣን ሥልጣን ሳይሰጠው አይቀርም ብሎ ማፈግፈግ ይጀምራል:: ግማሹ ሊያደርግም ላያደርግም ይችላል በሚለው ሀሳብ ይዋልላል:: ከአቋሙ ዝንፍ የማይለው መስፍን ነው::

"አንተን ብሎ ጢንዚዛ አድራጊ! አንተን ብሎ አምበጣና ፌንጣ አድራጊ! ና አድርገኛ?" ይልና ኮሌታውን ጨምድዶ ከተቀመጠበት ያነሳዋል:: ገላጋዮች መሃል ገብተው እስኪያስለቅቁት "በአማኑኤል!" ብሎ መማፀኑ አይቀርም:: የተለመደ ትዕይንት ነው::

ማርክስ ሳይሆን የኢሉሚናቲ (የሰይጣን አምላኪዎቹ የምሥጢር ማህበራት) መስራቹ አዳም ዌሻፕት መሆኑን አላወቀም::

"ሦስና አዳም ዌሻፕት ከሠባ ዓመት በፊት በሮዝቻይልድ ቤተሰብ ትዕዛዝ የነደፈውን እና በወረቀት ላይ ያሰፈረውን ማስታወሻ ነው ማርክስ ብሪትሽ ሙዚየም በሚገኘው የማንበቢያ ክፍል ዳግም የገለበጠው:: የጋሪ አለንን "None Dare Call it Conspiracy" ብታነቢ እውነታው ላይ ትደርሽበታለሽ:: ያን ጊዜ ኢየሱሳውያን በማርክስ ተጠቅመው በኢትዮጵያና በመላው ዓለም እግዚአብሔር የለም የሚል እምነትን ማስፋፋት ይፈልጉ ነበር:: ኢየሱሳውያን የማርክስን ብሩህ አእምሮ የተረዱትን ያህል እግዚአብሔር የለም የሚለውን እምነት በፖለቲካ ዘይቤ ስም፣ በርዕዮት ዓለም ስም በኢትዮጵያና በቀሪ ሶሻሊስት ሀገሮች ውስጥ ማስፋፋት እንደሚችሉ እርግጠኞች ነበሩ:: ለጊዜውም ቢሆን ተሳክቶላቸዋል:: ከፖለቲካ አጀንዳው ጀርባ ያለውን ድብቅ ሴራ ያልተገነዘበው ደርግ በሰማያዊው የደንብ ልብስ ታንቆ ከእኔ በላይ ፖለቲከኛ ላሳር አለ::

"በቀይሽብርና በነጭ ሽብር ስም ወንድምን ከወንድም፣ እህትን ከወንድም፣ አባትን ከልጅ፣ ባልን ከሚስት አፋጀ:: የነማርክስ ሰይጣን ምስ ደም ነበረ! የማርክስ ደቀመዝሙሮች የነበሩት እነሌኒን ሀሳቡን ተቀብለው በመላው ዓለም አስተጋቡት:: ለዓመታት ዘመሩት:: በማርክስ (ከአዳም የተገለበጠ) ኮምዩኒስት ማኒፌስቶ ንድፈ-ሀሳብ የነሆለለው «ጓድ» ቭላድሚር ኢሊች ሌኒን ሀሳቡን አሻሽሎ የተከታዮቹ መመሪያ አደረገው:: የማርክስ አስተምህሮት ከሌኒን አልፎ የጆሴፍ ስታሊንና የሊዮን ትሮትስኪ «ቅዱስ መመሪያ» ሆነ:: አብዮተኛው ደርግም «ዜጎቼስ ለምን ይቅርባቸው?» ሲል ትን እስኪለን ጋተን:: ሳናውቅ ለተወሰኑ ዓመታትም ቢሆን የኢሉሚናቲዎችን ሀሳብ ተግባራዊ አድርገን እሮብ እና አርብ መጾም ተውን:: የሚያምና በእግዚአብሔር የሚያምን አብዮተኛ አይደለም አልን:: የሰይጣን አምላኪዎች አጀንዳ ማስፈፀሚያ ሆንን:: ማንነታችንን ትተን ሌሎችን ለመምሰል ቁም ስቅላችንን አየን:: መንገዳችንን ትተን በሌሎች ጎዳና ላይ ፈሰስን::

"ፈጣሪያችንን ስለካድን፣ መጾም መፀለይ ስለተውን፣ እርስ በእርሳችን ስለተባለቅን ማርክስና ሰይጣን ጨፈሩ:: በአብዮታዊ ወኔ ዘመሩ:: በማርክስ ስም በኢየሱሳውያን ሴራ መረብ ተጠልፎ የወደቀው ደርግ ገብቶትም ይሁን ሳይገባው«አብዮት» በሚሉት የጥቅመኞች ጨዋታ ጎራ ለይቶ ተፋጀ:: የአንድ ሀገር ልጆች ለሌሎች ጥቅም እና ትርፍ ሲሉ ዜጎቻቸውን በቡድንና በፓርቲ ከፋፍለው አዋጉ:: አቋሰሉ:: ደም አፋሰሱ:: ኢትዮጵያ የምትባል ምስኪን ሀገር በማርክስ አለቆች ሴራ (ሠይጣንን ጨምሮ) ለህይወትና ለንብረት ኪሳራ ተዳረገች:: እድገቱ ቀርቶ የነበረኝ በተባረከልኝ ስትል አነባች::

"ይህ ታሪክ እንዳይደገም ነው መሪዎቻችን ሁሌ ሰው ላይ መንጠልጠላቸውን መተው ይኖርባቸዋል ስል የምጮኸው:: የዘመኑ አከናፊያችን ደግሞ ቻይና ሆናለች:: እፍ የሚያደርግ ፍቅር ይዞናል:: የእሷንስ የጀርባ እቅድ ማን አወቀ? ለመሪዎቻችን ልቦና ይስጣቸው ከማለት ውጭ ምን ይባላል? የዚህችን ሀገር እምነት፣ ባህልና ወግ መፈራረስ የሚናፍቁ በየት በኩል እንደሚመጡ አታውቂም:: ትላንት የፈጣሪ ታማኞች ሆነው ያየሻቸው ነገ የሰይጣን ተከታይ ሆነው ትመለከቻቸዋለሽ:: ልክ እንደማርክስ:: በወጣትነት ዘመኑ ክርስትያናዊ መንገድ ይዞ ይጓዝ የነበረውና «The Union of the Faithful with Christ» በተሰኘው የመጀመሪያ መንፈሳዊ ስራው የሚታወቀው ማርክስ በብርሃን ፍጥነት ተገልብጦ የሰይጣን አገልጋይ ይሆናል ብሎ ያሰበው ነበር? በፍጹም! እና ልጄ ሦስና ዛሬ የምታምኚው ሀገር፣ የምታምኚው መሪ የለም:: ይህች ምስኪን ቅድስት ሀገር የብዙዎች ትኩረት ናትና የምታምነው ፈጣሪዋ ይጠብቃት"

"አሜን!" የሚለውን ቃል በውስጧ ደጋገመችና በረዥሙ ተነፈሰች:: የቤት ስራዋ ክብደት ከወዲሁ ታይቷታል። ሲሰያዩ ጨልም ነበር::

# -13-

## ደቡባዊ የአንታርክቲክ አካባቢ፣ አንታርክቲካ

"ዛሬ" አለ ማርዮ ኖኤል ፐሪስኮት ፍጹም በሆነ ደስታ ተውጦ፡ "የጌታችን የማርዱክ ራ ሉሲፈር አስደሳች ስፍራ ወደሆነው የአዲስ ትውልድ ጣቢያ እንጓዛለን" ተከታዮቹ ላይ ጥድፊያና ጉጉት ተመለከተ፡፡ ልዩዋ የግል አውሮፕላን ከፍሎረንሥ የሚነሱ እንግዶቿን ጭና ወደደቡባዊ ዋልታ ለመብረር በዝግጅት ላይ ነች፡፡ የውቧ ከተማ ፍሎረንስ ዓለም ዓቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ጣቢያ አሜሪጎ ቬሥፑሲ ትከሻቸው በሚከብደውና የብዙ ሰዎችን ትኩረት በሳቡት «ታላላቅ ሰዎች» ተጨናንቋል፡፡ እነማን እንደሆኑና ወዴት እንደሚሄዱ ከራሳቸው በስተቀር ማንም አያውቅም፡፡ ከባለ አምስት ኮከቡ ሳቮይ ሆቴል ተነስተው አውሮፕላን ማረፊያ እስኪደርሱ የብዙዎችን ቀልብ ስበው ነበር፡፡

አንታርክቲካ ድረስ 15,270 ኪ.ሜትር ርቀት እንደሚጠብቃቸው ቢያውቁም ከወዲሁ ድካም አልተሰማቸውም፡፡ መቶ አስራ ሰባቱም እንግዶች አውሮፕላኗ ላይ ተሳፈሩ፡፡

በጉዟቸው እጅግ ደስተኞች ነበሩ፡፡ ከሁለት ቀን ተኩል በረራ በኋላ አብዛኛው ምድሩ በበረዶ ከተከበበው አንታርክቲካ ደረሱ፡፡ በማዕከሉ ውስጥ ካሉት ፍጡራን በስተቀር ሰው አልባ ቦታ ነበር፡፡ በአብዛኛው በውሃ የተከበበው የመሬት ክፍል እስከ ደቡብ አሜሪካ እንደተዘረጋ ያስረዳቸው ማርዮ ኖኤል ፐሪስኮት ጊዜ ካላቸው ታሪካዊዎቹን የለሜየር ቻናል፣ ፓራዳይዝ ሀርበርንና ወደሙዚየምነት የተቀየረውን የቀድሞውን የእንግሊዝ



የምርምር ተቋም እንደሚያስጎበኛቸው ቃል ገባላቸው፡፡ የገባላቸው ቃል ይህን ብቻ አልነበረም፡፡ ለአይን የሚስቡ የማይበሩ የዋልታ ወፎችን (ፔንግዊንስ)ም አሳያችኋለሁ ብሏቸዋል፡፡

በረዶ ላይ በተቸከሉ ግዙፍ ብረቶች ላይ ተንጠልጥሎ የተሰራው ግዙፍ ማዕከል ከቀይ፣ ነጭ እና ሰማያዊ ማይክ የተሰራ ነው፡፡ በውጭ በኩል በትልልቅ ፊደላት «የማርዱክ ራ ሉሲፈር አዲስ ትውልድ» የሚል ጽሁፍ ሰፍሮበታል፡፡ ጎብኝዎቹ በኖኤል ፐሪስኮት እየተመሩ ወደውስጥ ሲዘልቁ ቁመታቸው ከሦስት ክንድ የማይበልጥ፣ ጭንቅላታቸው ገንቦ የሚያክል እና የሚናገሩት ቋንቋ እንግዳ ስሆነ ሰው የማይገባ መንጋ ህጻናት ስፍራውን በጨኸት አናጉት፡፡ ደስታ መሆኑ ነው፡፡ ከሶስት መቶ የማያንሱትን እስፈሪ ህጻናት የተመለከቱት የልዑካን ቡድን አባላት የሚገቡበት ያጡ ይመስል ዙሪያቸውን በፍርሃት ቃኙት፡፡

"ተረጋጉ!" አላቸው ማርዮ ኖኤል ፐሪስኮት ፍርሃታቸውን ስለተገነዘበ፡፡ "ተረጋጉ! ከፀብ የራቁ የነገዋ አዲስ ዓለም ተረካቢ ህፃናት በመሆናቸው ልትወዷቸውና ልታቀርቧቸው እንጂ ልትፈሯቸውና ልትሸሿቸው አይገባም"

አባላቱ ሳይወዱ በግዳቸው እየገለፈጡ አጠገባቸው ያገኙትን አስፈሪ ህፃን ገንቦ ጭንቅላት ማሻሸት ጀመሩ፡፡ ህፃናቱ ለእንግዶቹ መቀበያ ያጠኑትን መዝሙር የሚያቀርቡበት ሰዓት በመድረሱ ተጠጋግተው ተሰለፉና ከእነሱ ይወጣል ተብሎ በማይጠበቅ ወፍራምና ሰቅጣጭ ድምጽ አካባቢውን አናወጡት፡፡

**ሉ! ሰንጋ ጃራ ቦንጋ ካራ**
**ቢጂ ቲጺ ማርዱክ ራ**
**ዛንዶር አርዴ ሌቪ ቢሲ**
**ማርዱክ ራ ቲቢ ሊሲ**
**ቲጺ ቲጺ ቢጂ ቃራ**
**ግሬ ዴሬ ማርዱክ ራ**
**ባል አስታርቴ ታሙዝ ሉሲ**
**ማርዱክ ራ አይ ዋና ሲ!**

ከልዑካን ቡድኑ አባላት መሃል የመዝሙሩ ትርጉም የገባው ሰው አልነበረም። ማርዮ ፐሪስኮት በደፈናው ተርጎመላቸው «ሎ!» እዩ ማለት ነው በአስፈሪዎቹ ህፃናት ቋንቋ ፍቺ። «ቲጺ» ኢትዮጵያ ናት። «ቃራ ትኩረትማለት ሲሆን «ብጂ» ዋንኛ እንደማለት ነው። «ግሬ ዴሬ» ሃምሳያ የማይገኝለት ታላቅ አምላክ ማለት ሲሆን «ባል»፣ «አስታርቴ»፣ «ታሙዝ» የሚሉት ቃላት ደግሞ ሌሎቹ የሉሲፈር መጠሪያ ስሞች ናቸው። የቀሪዎቹን ቃላት ፍቺ ሊተረጉምላቸው አልፈለገም። ሆን ብሎ ዘለላቸው። ምክንያቱን እሱ ያውቃል። በፍቺው መሰረት የመዝሙሩ ይዘት የሚከተለውን ይመስላል።

"እዩ! በደንብ ተመልከቱ። ሃምሳያ የሌለው ታላቅ አምላካችን ባል አስታርቴ ታሙዝ ራ ሉሲፈርን ምን ይሳነዋል? መሳውን ስነፍጥረት ሊቆጣጠርና በስሩ ሊያደርግ ትንሽ ቀርቶታል። ዋነኛ ትኩረቱ የሆነችው ኢትዮጵያ የሚኳት የእምነት ሀገር የእሱ ትሆን ዘንድ የምንችለውን ሁሉ እናደርጋለን። እንደሚሳካልን አንጠራጠርም። ማርዱክ ራ ሆይ ሁሌም ልናገኝህ፣ የፈቀድክልን እለት በአካል ልናይህ እንጓጓለን፣ ያንን ቀን በተስፋ ተሞልተን እንጠብቃለን"

ልዑካኑ ማብራሪያው ተዋጣላቸውም አልተዋጣላቸውም፣ መዝሙሩ አስደሰታቸውም አላስደሰታቸውም ማጨብጨብ ነበረባቸውና አጨበጨቡ። ማርዮ ኖኤል ፐሪስኮት ህፃናቱን እንደገና ለቡድኑ አባላት አስተዋወቀ።

"የነገዋ አዲስ ዓለም ተረካቢ፣ የማርዱክ ራ ሣይንሳዊ ውጤቶች እነዚህ ናቸው"

በልዩ ሳይንሳዊ ዘዴእንደዶሮ ጫጩት የተፈለፈሉ መሆናቸውን ለመገንዘብ ጊዜ አልወሰደባቸውም። ፐሪስኮት በአንድ ገለፃው ላይ "ልዩ እና ምስጢራዊ የሆነ የዳታ ማዕከል ያለው የቴክኖሎጂ ኩባንያችን በመጪው ትውልድ የአየር ትራንስፖርት ህግና ደንብ ስርዓት ላይ ትኩረት ያደረገ ነው። የአየር ትራንስፖርቱ ለጌታችን ለሉሲፈር ታዛዥ ይሆናል ብለን የምናስበውን መጪ ትውልድ ወደ አዲሱ የሰይጣን ዓለም ያለምንም ችግር



በፍጥነት ለማመላለስ እንደሚጠቅመን በማመን ያቀድነውና ወደተግባር ለመቀየር እየተጋንበት ያለ ፕሮጀክታችን ነው" ሲል ምስክርነትን የሰጠላቸው መጪ ትውልዶች እነዚህ መሆናቸው ነው ሲሉም ተገርመዋል።

ህፃናቱ ከፐሪስኮት ማብራሪያ በኋላ ተጠጋግተው መሬት ላይ ተቀመጡ። ተወካይ አድርገው የመረጡት ህፃን ንግግር ሊያሰማ ወደፊት መጣ። ዙሪያውን በኩራት ከቃኘ በኋላ ንግግሩን ቀጠለ።

"ጌታችንን ማርዱክ ራን እናገለግል ዘንድ የመጪው ትውልድ አውራ፣ የአዲሲቷ ዓለም ተረካቢ ሆነን (ምንም እንኳ በሳይንሳዊ ዘዴም ቢሆን) ወደምድር በመምጣታችን ኩራት ይሰማናል። አባታችንን ማርዱክ ራ ሉሲፈርን እናመሰግናለን። ወደፊት በምድራችን ላይ ለሚከሰቱ እና ለሚታዩ የማይታመኑ እውነቶች ፊት አውራሪዎቹ እኛ ነን። በታማኝነታችን እና በጥንካሬያችን ማርዱክ ራ የሚፈልገውን ውጤት በተግባር እናሳየዋለን። የወደፊቷ አዲስ ዓለም በማንሰስተው ጉልበታችን ራ እንደሚፈልጋት ትሆናለች"

ፐሪስኮት ራ እና ሲ የበዛባቸውን ቃላት ተርጉሞ ሲያበቃ የማዕከሉ የስብሰባ አዳራሽ በጨኸትና ጭብጨባ ተናጋ።

ከህፃናቱ ተወካይ በኋላ ንግግር ያደረገው ከሌላ ዓለም ፍጡራን እና የማይታወቁ በራሪ አካላት ጋር ልዩ ግንኙነት እንዳለው የተመሰከረለት የማርዱክ ራ ሉሲፈር «የሌላ ዓለም ፍጡራን ጉዳይ ምኒስትር» ዊልደን ሽናይደር ነበር።

"እነዚህን የሳይንስ ውጤቶች" አለ ወደአስፈሪዎቹ ህፃናት እያመለከተ "ከሌላ ዓለም ፍጡራን ጋር በማዳቀል ጌታችንን ሉሲፈርን የሚጠብቁ ጠንካራ ወታደሮች ለመፍጠር እቅድ ተነድፏል። ዓለም ብዥታ ውስጥ ነች። የሌላ ዓለም ፍጡራን እና የማይታወቁ በራሪ አካላት አሉ ብለው የሚያምኑ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች ቢኖሩም «የሉም» ሲሉ የሚከራከሩም በርካቶች ናቸው። አሜሪካና አጋሮቿ ከሳይንቲስቶቻቸው እንዲሁም ከውትድርና ሳይንስ ባለሙያዎቻቸው ጋር በመሆን የዓለምን ህዝብ

ለማደናገር የፈጠሩት ሴራ ነው ባዮችም አልጠፉም። ምንም ተባለ ምን የዓለም ህዝብ የሌላ ዓለም ፍጡራንና የማይታወቁ በራሪ አካላት ለማያምነው የዓለም ህዝብ የሌላ ዓለም ፍጡራንና የማይታወቁ በራሪ አካላት ከጌታችን ማርዱክ ራ ሉሲፈር ጋር በቅንጅት እየሰሩ መኖራቸውን፣ ከጌታችን ማርዱክ ራ ሉሲፈር ጋር በቅንጅት እየሰሩ መሆናቸውን እና ለአዲስ ዓለም አስተዳደር ተግባራዊነት ዋነኛ ተዋናዮች መሆናቸውን በተግባር ማሳየት ይኖርብናል። ያለበለዚያ ዓለም የማርዱክ ራ ኃይል ግዙፍነት የት ድረስ እንደሆነ አይገነዘብም።

"ለሌላ ዓለም ፍጡራን መኖር ከማንም በላይ ምስክሩ እኔ ነኝ። ማርዱክ ራን እንታዘዝም ካሉት ጋር በመዋጋቴ፣ ህብረታቸውን ካሳዩት ጋር ደግሞ መጪውን ዓለም በተመለከተ የጋራ ውል ስምምነት በመፈራረሜ በቅርበት አውቃቸዋለሁ። ከውል ስምምነታችን አንደኛውና ዋነኛው ማዕከሉ ውስጥ ከምትመለከቷቸው የማርዱክ ራ የሳይንስ ውጤቶች ጋር በማዳቀል ልዩ የሆነ የዘር ሀረግ መፍጠር ነው። ይህ የዘር ሐረግ ለማርዱክ ራ ሉሲፈር ፍጹም ታማኝ፣ የቅርብ ዘብ እና ዓለምን በአንድ ዓለም አስተዳደር ህግና ደንብ ትመራ ዘንድ ነገሮችን ከስር ከስር እየተከታተለ የሚያስፈጽም የተመረጠ ኃይል የያዘ ልዩ ስብስብ ይሆናል።

"የጌታችንን የማርዱክ ራ ሉሲፈር ትዕዛዝ ለማስፈጸም የሌላ ዓለም ፍጡራንን በጥልቀት ማጥናት ነበረብኝ። ለጥናት ስንቀሳቀስ በተፈጠረ ያለመግባባት ጭንቅላታቸው እንቁላል ከሚመስለው የሌላ ዓለም ፍጡራን ጋር መዋጋት ነበረብኝ። ብቻዬን እንዳልመሰላችሁ። አጋሮቼ አብረውኝ ነበሩ። የሌላ ዓለም ፍጡራኑ እና በራሪ አካላቱ ከምድር ገጽ በታች በሚገኝ ዋሻ እንደሚኖሩ ደርሰንበታል። እነዚህ ፍጡራን ለማርዱክ ራ ሉሲፈር አገልጋዮች መሆን እንደሚገባቸው በማመናችን ከእልህ አስጨራሽ ጦርነት በኋላ በቁጥጥራችን ስር አውለናቸዋል። ባደረግነው ጥናትም ሁሉም ተመሳሳይ ባህሪ እንደሌላቸው ደርሰንበታል። አንዳንዶቹ ክፉና መሰሪዎች እንዲሁም በጥላቻ የተሞሉ ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ ደጎች፣ የዋሆች እና ተባብሮ በመስራት የሚያምኑ በመሆናቸው ከእኛ፣ ከማርዱክ ራ አገልጋዮች ጋር እጅና ጓንት ሆነው ለመስራት ተስማምተዋል"

አባላቱ አጨበጨቡ። ህፃናቱ የተባለው ስላልገባቸው የትንሽ ፓፓዬ



ቅርጽ ያላቸውን አይኖቻቸውን አቁለጨለጩ።

ዊልዶን ሽናይደር ቀጠለ።

"የተስማሙትን በማዳቀል ነው ልዩ የሆነ የዘር ሀረግ ለመፍጠር እቅድ የያዝ ነው። አጋራችን ለመሆን ከተስማሙት የወደፊት የማርዱክ ራ ባሪያዎች ጋር እለት ከእለት ለመገናኘት በመላው ዓለም 7777፣ በአሜሪካ ደግሞ 777 በስራ ላይ የዋሉ የምድር ውስጥ ቤዞች (ሰፈሮች) ገንብተናል። እያንዳንዳቸው ከ77 እስከ 777 ሚሊዮን ዶላር ወጪ የጠየቁ ናቸው።

"እያንዳንዱ ሰፈር በምድር ስር ዋሻዎች ውስጥ በተሰሩ መተላለፊያ መንገዶች የሚገናኝ ሲሆን ሰፈር ከሰፈር የሚያገናኙ በማግኔት የሚሰሩ ባቡሮችም አገልግሎት ላይ ውለዋል። በሌላ ዓለም ፍጡራኑ ውስጥ አስራ አንድ ያህል የተለያዩ ዘሮች እንዳሉ የደረስንበት ቢሆንም ከእኛ ጋር ተስማምተው ለመስራት የተስማሙት ሁለቱ ብቻ ናቸው። ቀሪዎቹን በሂደት እንደምናሳምናቸው አንጠራጠርም። በእነሱ በኩል የጋራ ውል ስምምነቱን የፈረመው ቫል ቫሊያንት ቶር የሚባል ተወካያቸው ነው። ፔንታጎን ውስጥ ለሃምሳ ስምንት ዓመታት በታማኝነት እንዳገለገለ እና ከእኛም ጋር ተስማምቶ መስራት እንደማያስቸግረው ነግሮኛል። ቫል ቫሊያንት ቶር ስድስት የእጅ ጣቶችና ስድስት የእግር ጣቶች ያሉት ፍጡር ሲሆን ደሙ ኮፐር ኦክሳይድ እንደሆነ በምርምር አረጋግጠናል። በቅድሚያ ከእኛ የሳይንስ ውጤቶች ጋር የምናዳቅለው እሱን ይሆናል። ለማርዱክ ራ ሉሲፈር ባሪያ የሚሆን ምርጥ ዘር እንደሚሰጠን አንጠራጠርም"

የጋለ ጭብጨባ ተሰማ። ሽናይደር ንግግሩን መጨረሱን ስለተናገረ ማርዮ ኖኤል ፐሪስኮት መድረኩን ተረከበ።

"እስካሁን በተደረገው ገለፃ በቂ መረጃ እንዳገኛችሁ እርግጠኛ ነኝ። የተመረጡ መምህራን ትንሽም ቢሆን አሳሳቢ የሆነው የህፃናቱ ቋንቋ ነበር። የተመረጡ መምህራን ይመደቡላቸውና ለ6 ወራት ያህል የእንግሊዝኛ ቋንቋን ያጠናሉ። እንዲህ እንዲህ የመጀመሪያዎቹ አጥኚዎች አዲስ የሚወለዱትን ያስጠናሉ። እንዲህ እንዲህ እያለ እንግሊዝኛን የሚናገር የማርዱክ ራ ሉሲፈር ልዩ ዘር ዓለምን

ያጥለቀልቃታል"

ሌላ የጋለ ጭብጨባ።

ማርዮ ኖኤል ፐሪስኮት እና ተከታዮቹ ተጨማሪ ቀናትን በአንታርክቲካ መቆየት አላስፈለጋቸውም። በነጋታው የለሜየር ቻናልን፣ ፓራዳይዝ ሀርበርን እና የቀድሞውን የእንግሊዝ የምርምር ተቋም ጎብኝተው ወደፍሎረንስ ተመለሱ።



# -14-

## አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

እለተ እሁድ። ከቀኑ 8:45። የቲሱ መኝታ ተጋሪዎቹ ሰላም አልሰጥ ብለው እያማረሩት ነው። መተኛት ቢፈልግም አልቻለም። ራሱን ሲያጠፋ ምንም አልቀረውም።

"ጅብ! ኪስህን ለመሙላት ብለህ የፈረንጅ እግር ላይ ትነጠፋለህ?" መስፍን ነበር።

"ተኩላ! የነጠፈች ላም ምኗ ይታለባል? ደረቅ ጡቷን ስትመገምጉ ሼም ይሉት ነገር አታውቁምን!? ነጮቹስ እሺ። የለመደባቸው ዘራፊዎች ናቸው። አንተ ግን ምን ይሁን ብለህ ነው የሀገርህን ገመና ለነጫጭባ ለመሸጥ የተስማማኸው? ያውም ሰይጣንን ለሚያመልክ ነጫጭባ። ቱፍ! አንተ እና ቢጤዎችህ ተቆጥራችሁ ነው መቶ ሚሊዮን ገባን የምንለው?" አላምረው ብስጭትጭት ብሎ ተናገረ።

"እሱን በቅርብ አገኘነው እንጂ ሀገሪቱ የጅቦች ሀገር ከሆነች ቆይታለች። እሺ የት ሄደን እንኑር? ሀገራችን ውስጥ ከቤተሰቦቻችን ጋር ሰርተን እንዳንለወጥ ይህን መሳይ ጅቦች አናስኖር ብለውን ለስደት ይዳርጉናል። የጨካኞች ስለት በረሃ ውስጥ ይቀላናል። መንግስትም ጅቦችህን ማሰር ብቻ ሳይሆን ያለአግባብ የዘረፉትን፣ ህዝብ አስለቅሰው የገፈፉትን ንብረት ውረስና ለሌሎች መማሪያ አድርጋቸው ብንል መች ሰምቶን? እናቴ ትሙት እንዲህ አይነት ጅቦችና ሌቦችን ሳይ እሳት ልቀቅባቸው ነው የሚያሰኘኝ። እኔ ለምን ታሰርኩ? ሰው ለምን ደበደብኩ? ንዴቴ ከቁጥጥሬ ውጪ ሆኖ ደብድቤ። ሰው ደብድቤ።

እንደተሳሰሩ የገባኝ ቆይቼ ነው።

በእርሳቸው በማይበጠስ ኔትወርክ እንደተሳሰሩ የገባኝ ቆይቼ ነው፡፡ በእርሳቸው በማይበጠስ ኔትወርክ እንደተሳሰሩ የገባኝ ቆይቼ ነው፡፡

"አንድ ቀን አሳት ለብሼ አሳት ጎርሼ ሄድኩና ለምን ጉዳዬን እንደማትፈጽምልኝ ጠየቅኋት፡፡ ቀና ብላ እንኳን ሳታየኝ «ስራ ላይ ነኝ አትረብሸኝ» አለችኝ፡፡ ንቀቷ አበገነኝ፡፡ ማንም ምንም አያመጣም እብሪቷ አቃጠለኝ፡፡

"ጉዳዬን ትፈፅሚልኝ ዘንድ የግድ ሳንቲ ጉቦ መክፈል አለብኝ?" ጠረጴዛዋን በቡጢ ነረትኩት፡፡

"በህግ አምላክ አትስደበኝ፡፡ ያለስሜ ስም አትስጠኝ፡፡ ጉበኛ አትበለኝ" ተንጣጣች፡፡

"ጉብ ካልፈለግሽ ያለቀ ጉዳዬን ፈጽመሽ አሰናብቺኛ?"

"በህግ አምላክ ውጣልኝ?"

"የሆነ ደበሎ መሳይ ባልደረባዋ ደረቱን ነፍቶ መጣና

"ስራ ቦታ አትረብሽ" አለኝ፡፡

"ከእሷ ጋር ነው ያወራሁት፡፡ አንተ ምን ቤት ነህ?" «ምርጥ እስር ሙሰኞች» ስም ዝርዝር ቢሰጠፍ የመጀመሪያው ደረጃ የእሱ እንደሚሆን ሰዎች ሲያወሩ ሰምቻለሁ፡፡

"ስነ ስርዓት! አላስተናግድህም ስላለች ውጣላት"

"እናንተ ስለፈለጋችሁና ስላልፈለጋችሁ ነው የምስተናገደው?"

"እና ምን ልትሆን ነው?"

"የአባትህ ቤት መሰለህ?"

"የማነው እብሪተኛ!" አለና ሊገፈትረኝ ሞከረ፡፡

"ከዚህ በኋላ ንዴቴን መቆጣጠር አልቻልኩም፡፡ ሁለቱንም ወጥ በወጥ አደረግኋቸው፡፡ የእሱን ሁለት የፊት ጥርሱን አረገፍኩለት፡፡ የእሷን ግራ አይን አፈረጥኩላት፡፡ መስሪያ ቤቱ ተረበሸ፡፡ አንጀቱ ያረረ ባለጉዳይ «አሰይ በየቤቱ ወንድ አይጠፋም» ሲል አሞካሸኝ፡፡ ፖሊሶች ተጠርተው መጡ፡፡ ሊመቱኝ ሲከጅሉ "እንዳትነኩኝ ዋጋ ትከፍላላችሁ" አልኳቸው፡፡ ፈርተው ይሁን አይሁን አላውቅም ተውኝ፡፡

"ዛሬ ተፈርዶብኝ እስር ቤት ነኝ፡፡ ሳልወድ በግዴ ከቤተሰቦቼ ተለይቻለሁ፡፡ ዜጎችን በሙስና የሚያስጨንቁ ሌቦች ግን ዛሬም እያስለቀሱ የቢሮ ወንበር ያጣብባሉ፡፡ እነሱና ደሄ ጅብ ቁስ ተብዬ እንዲሁም መሰሎቻቸው ካልጠፉ የሰላማዊ ዜጎች መኖሪያ እስር ቤት ይሆናል" አለና አፍንጫው ውስጥ ወትፎት የነበረውን ሶፍት ቁሱ ላይ ወረወረው፡፡

የባንክ ኃላፊዎች፣ የፖለቲካ ሰዎች፣ ወዘተ... ልጆች እንደሆኑ በስራ ላይ በነበረበት ወቅት ተመልክቷል። በዚህ ሰበብ ከባለቤቱ ከዶክተር ሚሼል ፓዝዶር ጋር ከፍተኛ ግጭት ውስጥ ገቡ። ህመሙን መቋቋም አልቻለም። ወራዳ አባትነቱ ሰላም ነሣው። ያጣውን ሰላም ለማግኘት ሲል ቤንዚን አርከፍክፎ ላይተር ለኮሰ። ሆስፒታል በገባ በማግስቱ «ካሊፎርኒያ ፔሊካን»፣ «ዘ አድቮኬት» እና «ኤሮቲክ ኒውስ ኤንድ ሪቪው ካሊፎርኒያ ሰንዴይ»፣ ተመሳሳይ ዜና ይዘው ወጡ።

**"የቀድሞው የባህር ኃይል የመረጃ ክፍል ዋና ኃላፊ ሎውረንስ ፓዝዶር ራሱን አጠፋ!"**

ችኮላቸው ባለቤቱን ሚሼል ፓዝዶርን እጅግ አበሳጫት። በአስራ አንደኛው ሰዓት በተዓምር መትረፉን ጎኑ ሆና ያረጋገጠችው እሷ ናት። እያቃሰተ "ሚሼል ኃጢያቴ ከይቅርታ በላይ ቢሆንም እንደዚህ ሆኜ አትተይኝ። ማን አለኝ?" ሲል ተማጸናት። አንጀቷ ተንሰፈሰፈ። ውድ ልጃቸውን አሳልፎ ቢሰጥም ልትጨክንበት አልቻለችም። ይቅርታ አደረገችለት። በቅርብ የሚከታተለውን ዶክተር፦

"የሥራ ባልደረቦች ይጨካከናሉ?" ስትል ጠየቀችው።

"አልገባኝም" አላት። የተለያየ ሆስፒታል ውስጥ ቢሰሩም ስለእሷ ሰምቷል። ምስጉን የህክምና ባለሙያ መሆኗን።

"ቅኝ ታምቹ የህትመት ውጤቶች ቸኩለው ያወጡትን ዘገባ ተመልክተሃል። ባለቤቴ ግን በተዓምር ድኗል። ከሆስፒታል ደብቄ ይዤው እስከወጣ መዳኑን ማንም እንዲያውቅ አልፈልግም"

"ለምን?" ተገርሞ ጠየቃት።

"ምክንያቱ ለጊዜው ምንም አያደርግልህም"

ትክሻውን በግዴለሽነት ሰብቆ በሀሳቧ መስማማቱን ገለጸላት። ደጋግማ አመሰገነችው። የመዳኑ ወሬ እንዳይሰማ የተማፀናት ባለቤቷ እንደሆነ ግን አልነገረችውም። ብዙም ሳያገግም ደብቃ ይዛው ወጣች። እስከ ጥቁሩ



ታሪካቸው፣ ክፉውን እውነት እስከሚያስታውሳቸው ገመናቸው ካሊፎርኒያ ውስጥ መኖር አልፈለጉም። ሦስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሠላሳ ኪሎ ሜትር ተጉዘው ማንሀታን፣ ኒውዮርክ ገቡ። እዚህ ቦታ ማንም አያውቃቸውም። አዲስ መኖሪያ፣ አዲስ መስሪያ ቤት፣ አዲስ ወዳጆች። ሚሼል በስራ ልምዷ ከማንሀታን እውቅ ሆስፒታሎች አንዱ በሆነው ሌኖክስ ሂል ሆስፒታል በቶሎ ነበር ስራ ያገኘችው። ባለቤቷ ሎውረንስ ከአራት ወራት የህክምና ክትትልና ማገገም በኋላ ቤቱ ተቀምጦ እጁ ላይ የነበሩ መረጃዎችን ወደ መፅሐፍ ታሪክ መቀየር ጀምሯል። የፊቱ ገጽታ ሙሉ በሙሉ ተቀይሯል። የዱሮ ወዳጆቹ ቢያዩትም አያውቁትም። መልከ-መልካሙ ሎውረንስ የቫምፓየር ፊልም ገፀ-ባህርያትን መስሏል። በዚህ አይነት ሁኔታ ጊዜያት አለፉ። ለታሪኩና ለገጽታው መቀየር ምክንያት የሆኑትን ኃይሎች ሴራ ለማጋለጥ ለእራሱ ቃል ገባ። አንድ ሰው አስታወሰ። አድራሻውን ፈልጎ ማግኘት ይኖርበታል። ሴራቸውን በማጋለጥ ረገድ በጋራ ወሳኝ የሆነ ሚና እንደሚጫወቱ እርግጠኛ በመሆኑ መላ ሰውነቱን ደስታ ወረረው። መዳኑ እንዳይታወቅ የፈለገው ለዚህ ነበር።

***

ሚሼል ፓዝዶር በአጭር ጊዜ ውስጥ በምትሰራበት ሆስፒታል ዝነኛ ሆናለች። "ዶክተር ከእሷ ወዲያ" ተብላለች። ታካሚዎቿ በአብዛኛው እውቅ የሲኒማው ዓለም ኮከቦች፣ ስመ-ጥር የንግድ ሰዎች፣ ዘፋኞች፣ ፖለቲከኞች እና የምክር ቤት አባላት ናቸው።። በቁጥር የሚልቁት የግል ዶክተራቸው አድርገዋታል። ቤታቸው ውስጥ በሚያዘጋጁት ድግስ ላይ ይጠሯታል። ወዳጅነታቸውን ያሳዩዋታል። ይህም ሆኖ ያለፈ ታሪኳን የሚያውቅ አልነበረም። በዚህ ሁሉ ደስተኛ ብትሆንም ደስታዋ የተሟላ አይደለም። ልጇ ጃስፐር አጉድሎባታል።

ቢሮዋ ውስጥ በስራ ተወጥራ በነበረችበት አንድ እለት የጥሪ ካርድ ደረሳት። ከከተማው እውቅ ፖለቲከኞችና የህግ መወሰኛ ምክር ቤት አባላት ከአንዱ። ቢሮዋ ድረስ መጥቶ የሰጣት እራሱ ነው። ጥሪው ባለቤቷንም ይጨምራል። የሪፐብሊካን ፓርቲ አባሉ ኬኔዝ ቶማስ ፍላናጋን ካርዱን

ሠፈር»፣ «የነጋዴዎች ሰፈር»፣ «የሴተኛ አዳሪዎች ሰፈር»፣ «የገዳዮች ሰፈር»፣ «የዶክተሮች ሰፈር»፣ «የግብረ-ሰዶማውያን ሰፈር» የሚሉ ፅሁፎች በደማቅ ቀይ ቀለም ተጽፈው ተመለከቱ::

"እያንዳንዱ ሰፈር ውስጥ የሚገኙትን ህፃናት እንጎበኛለን" አለ ፐሪስኮት "እግረመንገዳችንንም ለማርዱክ ራ ሉሲፈር አገልጋይነት ብቁ መሆናቸውን እንገመግማለን"

ሰፈሮቹን መጎብኘት ጀመሩ:: በሺህዎች የሚቆጠሩት ህፃናት ሁለት መቶም፣ ሦስት መቶም እየሆኑ እንደየምድባቸው መጋዘን በሚመስሉ አዳራሾች የአእምሮ ቁጥጥሩ ሳይንስ ተግባራዊ እየተደረገባቸው ነው:: ጨካኙን ሳይንስ ተግባራዊ የሚያደርጉት ሳይንቲስቶች በአብዛኛው የናዚ አባላት የነበሩ መሆናቸውን ለባልደረቦቹ የነገራቸው ማሪዮ ኖኤል ፐሪስኮት ከሲ.አይ.ኤ የአእምሮ ቁጥጥር ቅርንጫፍ ማዕከላት የመጡ ባለሙያዎችም እንዳሉ አልደበቃቸውም::

"በነገራችን ላይ" አለ ፐሪስኮት በኩራት ደረቱን ነፋ አድርጎ "የበርካታ አይሁዳውያን ህፃናትን ህይወት ቅርጥፍ አድርጎ የበላው ጆሴፍ ሜንግልም ከአእምሮ ቁጥጥር ሳይንቲስቶቻችን ግንባር ቀደሙ ነበር"

መርፌ የሚወጉ፣ ኪኒን የሚውጡ፣ ልዩ መሳሪያ ጭንቅላታቸው ላይ ተገጥሞላቸው በኤሌክትሪክ ንዝረት አእምሯቸውን የሚነጠቁ፣ በብቁ ባለሙያ በሳይንሳዊ መንገድ የሁለት ሰብእና ባለቤቶች የሚሆኑ እና ሌሎችንም ተመለከቱ:: ህፃናቱ እንኳን ጎብኚ ዝምብ በአጠገባቸው ያለፈ አልመሰላቸውም:: በአእምሮ መነጠቅ ተግባር ላይ ስለነበሩ ዙሪያቸውን መገንዘብ የማይችሉበት ሁኔታ ላይ ናቸው:: በጎብኚዎች ምክንያት የአእምሮ መነጠቅ ስርአቱ ተጠናቀቀና ህፃናቱ በየምድባቸው ጠበቁ::

በቅድሚያ የተጎበኘው የጄኔራሎቹ ሰፈር ነበር:: እዚህ ምድብ (ሠፈር) ውስጥ ያሉት ህፃናት ተፈጥሮአዊ ዝንባሌያቸው ተጠንቶ ይህን ሰፈር የተቀላቀሉ ናቸው:: ለነገሩ ሁሉም ህፃናት ተፈጥሮአዊ ዝንባሌያቸው ተገምግሞ ነው እንደየዝንባሌያቸው በየሰፈሩ የተመደቡት:: በጄኔራሎቹ ሰፈር



ያሉትን ህፃናት የምታስተዳድረው ወይዘሮ ዞሃራ ጆራርድ እንግዶቹን እየመራች ማብራሪያ ትሰጥ ጀመር::

"እዚህ ሰፈር ያሉ ህፃናት ሁሉም ኃይለኞች፣ ግትሮች፣ ጨካኞችና ፍላጎታቸውን የሚጻረር ኃይል ቢመጣ መስዋእትነትን ከመክፈል ወደኋላ የማይሉ ናቸው:: በአንፃሩ የበላይ አለቃቸውን ትዕዛዝ ለመፈፀም ቅኖችና ፈጣኖች ናቸው"

ማርዮ ኖኤል ፐሪስኮት ደስ አለው:: እውነተኞቹ የማርዱክ ራ ወታደሮች እየደረሱለት እንደሆነ እርግጠኛ ሆነ:: እነዚህን ወታደሮች ለአቅመ ትዕዛዝ ሲደርሱ የትኛውንም ሀገር ውረሩ ብሎ ትዕዛዝ መስጠት ይቻላል:: በአንድ ሀገር ግዛት ገብታችሁ መፈንቅለ-መንግስት አካሄዱ፣ የአየር ድብደባ አድርሱ ቢባሉም ያለማንገራገር የሚቀበሉ ናቸው:: እጨ ጄኔራሎቹን በኩራት ቃኘት አደረገና ወደካህናት ሰፈር አመራ:: ተከታዮቹ የእሱ ፊት በደስታ ሲበራ የሚስቁ፣ በሀዘን ሲጨልም የሚተክዙ ነበሩ::

በካህናት ሰፈር የተቀበላቸው ምጥጥ ያለ ፊት ያለው ሰው ነው:: በዚያ ላይ ፈንጣጣ ወሮታል:: የጅል ፈገግታውን ካሳያቸው በኋላ ህፃናቱን አስጎበኛቸው::

"እዚህ ሰፈር ያሉ ህፃናት ሲናገሩ ዝግ ብለው ሲሆን አብዛኛውን ጊዜያቸውን በተመስጦ እና ለብቻቸው የሚያሳልፉ ናቸው:: ከእራሳቸው ጋር ሲነጋገሩም ይስተዋላሉ:: ፀሎት በማድረስ ላይ ይሁኑ አይሁኑ የሚያውቁት እራሳቸው ናቸው" አለ ፊተ መጣጣው ጆርገን ሄልሙት ሜርክል::

"እነዚህ" አለ ፐሪስኮት በልቡ "በሃይማኖት ስም የማርዱክ ራን እቅድ ተግባራዊ ለማድረግ ብቁ ሆነው የሚያድጉ ናቸው:: ለፀረ-ክርስቶስ ዘመቻችንም ወሳኝ የሆኑ ኃያላት ናቸው" በነጋዴዎቹ ሰፈር ያገኟቸው ህፃናት ለየት ያሉ ናቸው:: አንዳንዶቹ የግል ልብሳቸውንና ንብረታቸውን በሙሉ ገንዘብ እስካገኙ ድረስ ከመሸጥ የማይመለሱ ናቸው:: ንብረቶቻቸውን ወደጄኔራሎቹ እና ሴተኛ አዳሪዎች ሰፈር ወስደው ለመሸጥ ሙከራ ላይ ሳሉ በቁጥጥር ስር የዋሉ ህፃናት እንዳሉ አስተዳዳሪያቸው ኬቨን ሂርጌመስ

ተናገረ::

"እነዚህ የዓለምን ውድ ነገር ሁሉ ለራ ጥቅም ሲሉ ከመሸጥ የማይመለሱ በመሆናቸው እንከራባቸዋለን"

ተከታዮቹ የፕሪስኮትን ንግግር ማድነቃቸውን በጭብጨባቸው ገለጹ:: በቀጣይነት የተመለከቱት የሴተኛ አዳሪዎችን ሰፈር ነበር:: ውበታቸው የሚያፈዘው ሴት ህፃናት ጭናቸው ላይ የሚቀር አጭር ቀሚስ ለብሰዋል:: አይኖቻቸውን እያስለመለሙ እንግዶቹን ተመለከቷቸው::

"በየጊዜው ወደ ወንዶቹ ሠፈር ካልሄድን ብለው ስለሚያስቸግሩ በግድ ነው የያዝናቸው" አለች የሠፈሩ አስተዳዳሪ ሄለን ብራውን::

"አቤት ሲያድጉ!" አለ ፕሪስኮት እያደነቀ:: "በገፍ የሚቆጠሩ የወሲብ ፊልሞች ተመርተው ለተመልካች ይቀርባሉ:: አዳሜ ያንን እያየ ስሪያ በስሪያ ይሆንና የኤች አይ.ቪ ኤድስ በሽታውን ቁጥር በእጥፍ ይጨምረዋል:: አንደኛው ዓላማችን ይህ አይደል! ህዝቡን በበሽታ መቀነስ:: ምርጥ ምልምሎቻችን ናቸው:: ምን ዋጋ አለው? እነሱ ሲደርሱ እኛ እናረጃለን ወይ እንሞታለን"

ወደገዳዮቹ ሠፈር አመሩ:: አስተዳዳሪው እራሱ ገዳይ ይመስላል:: ዴልታ የሚል ፅሁፍ የተፃፈበት ቲ-ሸርት የለበሰ ረዥምና ወፍራም ሰው ነው:: "ሲሞን በርኔት" ሲል ራሱን አስተዋወቃቸው::

"ከመሃላችሁ ፍቃደኛ የሆነ ሰው ካለ በሰከንድ ውስጥ እንዴት መግደል እንደሚቻል ያሳዩዋችኋል:: አብዛኛውን ሰዓታቸውን የሚያጠፉት የግድያ ፊልሞችን በመመልከት ነው"

ፕሪስኮት ሰውዬውን ገላመጠው:: "ፍቃደኛ ካለ እንዴት መግደል እንደሚቻል ያሳዩዋችኋል" የሚለው ድፍረት አዘል ንግግሩ አላስደሰተውም:: "የግድያ ፊልሞችን በመመልከት አብዛኛውን ጊዜያቸውን ያሳልፋሉ" የሚለው ንግግር ግን ተስማምቶታል::

"ልጆቼ ቶሎ እደጉና ለተልዕኮ ትሰማራላችሁ:: ያስቸገረ የሀገር መሪ፣



ራን ያወገዘ የሃይማኖት አባት፣ በአጠቃላይ ከእኛ በተቃራኒ የቆመን ማንኛውንም ግለሰብ በሰከንድ ሲጥ ስታደርጉ ማየት እንዴት ልብን በሀሴት ይሞላል? እውነተኛዎቹ የራ ልጆች ስለሆናችሁ አባታችሁ እንዴት ይደሰትባችሁ!? እንዴት ይኮራባችሁ!?"

ወደ ግብረሰዶማውያኑ ሰፈር አመሩ:: የተቀበላቸው አስተዳዳሪ ወንድ ቢሆንም ከንፈሩን ቀይ ቀለም የተቀባ፣ ቅንድቦቹን የተኳለና ሲያወራ እጆቹን እያፍተገ የሚቅለሰለስ ነበር:: "ሉትዘር ሁግስ" ሲል እራሱን አስተዋወቃቸው:: እሱን መሰል ህፃናት መጋዘን መሳዩን አዳራሽ አጨናንቀውታል:: የፕሪስኮት ተከታዮች እስካሁን ከጎበኟቸው ሰፈሮች ይህኛውን ወደውታል:: ህፃናቱን የመመኘት ከፍተኛ ፍላጎት በፊታቸው ላይ ይነበባል:: ይህን የታዘበው ማርዮ ኖኤል ፕሪስኮት እንዲህ አላቸው::

"እንግዲህ ቅሌታሞች አትሁኑ:: እነዚህ ለልዩ የራ አገልግሎት በማዕከል ውስጥ ያሉ ስለሆኑ አመላችሁን ወደየሰፈራችሁ ስትመለሱ ታስተናግዱታላችሁ"

በህፍረት መሬት ተከፍታ ብትውጣቸው ደስተኞች ነበሩ:: በመጨረሻ የጎበኙት የዶክተሮችን ሰፈር ነበር:: ራሷን "ሊዛ ጆርዳን" ብላ ያስተዋወቀቻቸ ውና ነጭ የዶክተሮች ካፖርት የለበሰች ውብ ሴት ህፃናቱን ታስጎበኛቸው ጀመር::

ሁሉም ላይ ከእድሜያቸው ጋር የማይመጣጠን ብስለት ይታያል:: አንዳንዶቹ አይናቸው ላይ ሰክተው ጥቃቅን ህዋሳትን ከሚመለከቱበት ማጉያ መነፅር ውጭ ለምንም ነገር ደንታ ያጡ ይመስላሉ:: አንዳንዶቹ ደግሞ ጥራዛቸው ሰፊ የሆኑ መጻህፍት እያገላበጡ ነበር::

ፕሪስኮት እነዚህንም በተከታዮቹ ፊት መረቃቸው "እደጉ ተመንደጉ! በዓለም ላይ ለሚፈፀመው የህክምና ቅሌት ዋናዎቹ ተዋናዮች እናንተ ትሆናላችሁና የምታገለግሉት ማርዱክ ራ ሉሲፈር ይርዳችሁ:: የዓለምን ህዝብ ቁጥር በህክምና ሰበብ የምታመናምኑልን እናንተ ናችሁና ቶሎ ድረሱልን"

"አሜን!" አሉ ተከታዮቹ፡፡

ፕሪስኮት በጉብኝቱ ደስተኛ ነበር፡፡ የአእምሮ ቁጥጥር ማዕከላቱ ተግባራቸውን በሚገባ እየተወጡ እንደሆነ አምኗል፡፡ ራን የሚያገለግል አዲስ ትውልድ መጪ ጊዜን በሀሳቡ እየና በደስታ ተፍነከነከ፡፡ ተከታዮቹ ገለፈጡለት፡፡ ቅር የተሰኘበት ጉዳይ ቢኖር ከህፃናቱ መሃል ኢትዮጵያውያን ያለማየቱ ነበር፡፡



# -18-

# ፓልማ፣ ማሎርካ

በካርሎ ዛጋሚ ፋውንዴሽን መስስተኛ ስፋት ባለው ቢሮአቸው ውስጥ የተሰባሰቡት የምስጢር ማህበራት ሴራ አክሻፊዎች ከዓለም ህዝብ ስለተደበቀውና ብዙ የማጭበርበሪያ ሀሳቦች ተካተውበታል ተብሎ ስለሚታመነው መፅሐፍ እየተወያዩ ነው፡፡ ሁሉም ከዚህ ቀደም የሚተዋወቁ ናቸው፡፡ በተለያዩ ቅርንጫፎች ውስጥ በኢሉሚናቲ አባልነት ሲያገለግሉ የነበሩ፡፡ ዛሬ ካርሎ ዛጋሚ በ "The As Hermetis Foundation" ስር አሰባስቧቸዋል፡፡

"ሰማያዊው መፅሐፍ"የራ እና ተከታዮቹ የአምልኮ መፅሐፍ እንደሆነ ያውቃሉ፡፡ ለክርስቲያኖች መፅሐፍ ቅዱስ የህይወታቸው መመሪያ እንደሆነ ሁሉ ለራ እና ለተከታዮቹ ሰማያዊው መፅሐፍ የህይወታቸው መመሪያ ነው፡፡ እያንዳንዱ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት በኋይት ሃውስ የግል ክፍሉ ውስጥ ይህ መፅሐፍ እንዳለው ዛጋሚ እና ባልደረቦቹ ያውቃሉ፡፡

ሁለት ሺህ ዘጠና ሰባት ገጽ እንዳለው የተነገረለት ይህ መፅሐፍ በውስጡ ኢትዮጵያንና ሩሲያን ጨምሮ መሰል የክርስትና እምነት ተከታይ ሃገራት የሚጠፉበትን ምስጢር እንዳካተተ የሚናገሩ ቢኖሩም ተቃራኒዎቻቸው በዚህ ሀሳብ አይስማሙም፡፡ ይልቅ አሜሪካ በሰይጣናዊ ኃይል እየተመራች ዓለምን የምትገዛበት ምስጢር ተካቶበታል ሲሉ ይከራከራሉ፡፡

ይህን መፅሐፍ በኢሉሚናቲ ማህበር ውስጥ ሳለ ከአንድ የአሜሪ

ለማብራራት ሞከረ።

አዳም ዌሻፕት፣ ኤሊፋስ ሌቪ፣ (አልፎንስ ልዊስ ኮንስታንት በሚለው ስሙም እንደሚታወቅ አስታወሰ) አልበርት ፓይክ፣ ጁሴፔ ማዚኒ፣ ሄሌና ብላቫትስኪ፣ አሊስተር ክሮውሌይ፣ አንቶን ሌቪ እና ሚካኤል ኢኪውኖ።

"ሁሉም የሠይጣን ደቀመዛሙርት ናቸው" ሲል አሰበ። "ማርዱክ ራ ሉሲፈር የአገልግሎታቸውን ዋጋ አይዘነጋም። እንደየአስተዋጻኦቸው ይከፍላቸዋል። የምድራችን ዘላለማዊ ጀግኖች ናቸው"

እነሱን መሆን ተመኘ። እነሱን ሆኖ ለማርዱክ ራ ሉሲፈር ሚዛን የሚደፋ አስተዋፅኦ ለማበርከት ጓጓ። ከሀሳቡ የመለሰው "እንኳን ደህና መጣችሁ" የሚለው የካቴድራሉ አስተዳዳሪ ቄስ ኤርዊን ግርሃም ድምፅ ነው። ኤሪዊን ግርሃም ዋና ዋናዎቹን እንግዶች በየተራ እየጨበጠ ወደተያዘላቸው የክብር ስፍራ መሯቸው። ካቴድራሉ የተገነባው አስር ሺ ስድስት መቶ አስር ስኩዌር ስፋት ባለው ቅፅር ግቢ ውስጥ ነው። ቅፅር ግቢውን ያስዋቡት የዕድ እና የወይራ ዛፎች የፀሐይ መከላከያ ጥላ ሆነው ያገለግላሉ። ከካቴድራሉ ፊት ለፊት ላይ በሚገኘው ሰፊ መስክ ላይ ፀሐይ መከላከያ ነጫጭ ግንጥላዎች ተዘርግተዋል። እንግዶች ሲያሻቸው ሻይ ቡና የሚባባሉበት ስፍራ ነው። ካቴድራሉ በጽድ፣ በወይራ እና ሌሎች በርካታ የዛፍ አይነቶች ስለተሸፈነ ከውጭ ሰው እይታ የተሰወረ ነው።

"ጥቂት ደቂቃዎች ለማረፍ" በሚል ሰበብ መስኩ ላይ ሻይ ቡና ሲባባሉ የቆዩት እንግዶች የአምልኮው ሰዓት በመድረሱ ወደካቴድራሉ እንዲገቡ ተነገራቸው። ገብተው ቦታቸውን ያዙ። አብዛኞዎቹ እንግዶች ዓለም በተደበቀው አፀያፊ ሰብእናቸው የሚያውቃቸው አይደሉም።

የእንግሊዝ፣ደች እና ቤልጂየም ንጉሣውያን ቤተሰቦች ከመጀመሪያው ረድፍ ላይ ተቀምጠዋል። ከእነሱ ኋላ ሊቀጳጳስ ፍራንሲስ በሚለው የሀሰት ስሙ የሚታወቀው ማርክ በርጎግሊዩ አለ። ጆሴፍ ራትዚንገር እና ጀምስ ዌልባይ ከእሱ ትይዩ ያሉትን ወንበሮች ይዘዋል። እነዚህ ግለሰቦች በየዐመቱ በሚደረገው የብላክ ማስ የአምልኮ ስነ-ሥርዓት ላይ በርካታ ህፃናትን



በመድፈር ሪከርድ የያዙ ናቸው። የካቴድራሉ መብራት ድርግም አለ።

"ከጌታችን ማርዱክ ራ ሉሲፈር ጋር በመንፈስ የምንገናኝበት ሰዓት ደረሰ" አሉ ተሳታፊዎቹ በልባቸው። እጅግ በርካታ ቁጥር ያላቸው ጥቋቁር ሻማዎች ተለኮሱ። የተገለበጠ መስቀል የተለጠፈባቸው ቀያይ ቀሚሶችን የለበሱ አገልጋዮች በሰልፍ ሲገቡ ታማኝ አሽከሮች ህፃናትን እየታቀፉ መግባት ጀመሩ። የህፃናቱ ለቅሶና ጩኸት ሰሚ አልነበረውም። እድሜያቸው ከአምስት ዓመት እስከ አስራ ሦስት የሚደርስ ነበር።

"ከብራንትፎርድ የህንድ አዳሪ ትምህርት ቤት የተሰረቁ" አለ ማርቲን ሮበርት። ቀደም ብሎ መረጃው ደርሶታል። ህፃናቱን መድፈሩ እና ማስቃየቱ ቀጠለ። ከሰው አጥንት የተሰራ እጀታ ያለው ቢላዋ የያዘ አገልጋይ ከፍ ወዳለው መድረክ ሲያመራ ከዚህ በኋላ ምን ሊፈጸም እንደሚችል የሚያውቁት የሥነ-ስርዓቱ ተሳታፊዎች ተረኛ ለሆነው ታራጅ ህፃን ፀሎት አደረሱ።

"ለሉሲፈር በግኑት ክብር ስለበቃህ ነፍስህን በመንግስቱ ከጎኑ ያስቀምጠው አሜን" ቀጣዩ ሥነ-ሥርዓት ወሲባዊ አምልኮ የሚፈጸምበት ነበር። ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ነው። ሰይጣን በኢየሱስ ላይ ተቀናጅቶታል ብለው ለሚያምኑት ድል መታሰቢያነት የሚሆን የወሲብ ስርዓተ አምልኮ። ወንድ ሊቀ-ካህናትና ሴት ሊቀ-ካህናት እጅ ለእጅ ተያይዘው ወደፊት ሲወጡ ቄስ ኤርዊን ግርሃም፦

"አባታችንን ሰይጣንን እና እናታችንን ሔዋንን ለሚወክሉት ሊቀካህናቶቻችን ሞቅ ያለ ጭብጨባ" አሉ። ሴቶች በእልልታ ወንዶች በጭብጨባ ካቴድራሉን አናወጡት። የሰይጣንና የሔዋን ተወካዮች በገሃድ ወሲብ መፈፀም ጀመሩ። የተለመደ ትዕይንት ነበርና ተሳታፊዎቹ እያጓሩ ጮኹ። ሥርዓቱ ዘለግ ላለ ጊዜ ከተካሄደ በኋላ በኤርዊን ትዕዛዝ ተቋረጠ።

"ለዛሬ ይበቃል" አሉ ቄስ ኤርዊን። "የሉሲፈርን ኃያልነት በስኑ ሥርዓታችን መስክረናል"

ሞቅ ያለ ጭብጨባና እልልታ:: ወሲብ ፈፃሚዎቹ ልብሶቻቸውን እየለበሱ ወደ መቀመጫቸው ተመለሱ:: የዚህ ዓመቱ የብላክ ማስ ሰይጣናዊ የአምልኮ ስነ-ሥርዓት በዚህ አይነት መልኩ ተጠናቀቀ:: ከመበታተናቸው በፊት ቁስ ኤርዊን እንዲህ አሉ::

"ተምሳሌትነቱ መቼም ይገባችኋል:: ከወሲባዊ ተራክቦ የሚገኘውን ደስታ ለሔዋን እና ለሰይጣን የገለፀላቸውን ሉሲፈርን ለማስታወስ ነው"

ታዳሚዎቹ በገብቶናል ስሜት ራሳቸውን አወዛወዙ::

"እንደሉሲፈር ፍቃድ ይህን የአምልኮ ስርዓት በሩሲያና በኢትዮጵያ አስርገን የማስገባት እቅድ አለን"

ተጨበጨበላቸው::



# -20-

## ማንሀታን፣ ኒውዮርክ

ሎውረንስ ፓዝዶር እንደተመኘው ከኬኔዝ ቶማስ ፍላናጋን ጋር ጥብቅ ወዳጅነት በመመስረቱ ደስተኛ ሆኗል:: በቤቱ ከተካሄደው የእራት ግብዣ በኋላ እየተገናኙ ሀሳብ መለዋወጥ ጀምረዋል:: ኬኔዝ የሎውረንስን እዋቂነት ወዶለታል:: በብዙ ነገሮች ላይ ያለው ግንዛቤ አስደንቆታል:: በፖለቲካው መስክ የማያውቀው ነገር የለም:: ግራ ሳጋቡት ነገሮች መፍትሔ የሚሻው ሎውረንስን በማማከር ሆኗል::

ሎውረንስ ከኬኔዝ ጋር ተቀራርቦ ወዳጅነት ቢመሰርትም እውነተኛ ማንነቱን አልነገረውም:: ከዚህ በፊት ከባለቤቱ ጋር በሌላ ከተማ እንደሚኖር፣ ፋብሪካ ውስጥ ይሰራ እንደነበርና ድንገት ከተከሰተው የእሳት አደጋ በኋላ መኖሪያውንም፣ ሥራውንም እንደለቀቀ የነገረውን እምና ተቀብሎታል:: በሀዘኔታ ስራ ልፈልግልህ ቢለውም የእራሴ እቅድ አለኝ በሚል ሰበብ ሳይቀበለው ቀርቷል::

አንድ ቀን ኬኔዝ እንዲህ አለው::

"እኔ የምልህ ሎውረንስ ከእኔ ጋር ለጉብኝት ወጣ አትልም?"

"ወዴት?" አለ ሎውረንስ እድሉን ለመጠቀም በመፈለግ::

"የቦሂሚያ ጫካ ስነ-ሥርዓት ላይ ለመገኘት ፍቃደኛ ከሆንክ አብረን መሄድ እንችላለን"

